ከመንገድ ገለል እናደርጋቸዋለን[2]። እንግዲያው ወደዚያው እንዝለቅ:—

ሰው ፍጹም አይደለም። ማናችንም ብንሆን፣ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ እንስታለን፣ እንሳሳታለን። "ሰው ሆኖ አይስት አንጨት ሆኖ አይጤስ የለም" የሚለው አገርኛ ቢሂል፣ ይህን የሰውን ልጅ የፍጽምና ረሀብ፣ በርኅራኄ የሚያስታውስ ይመስለኛል። ሰው ሁሉ የሚስት/የሚሳሳት ቢሆንም፣ ባለማወቅ ልስት እችላለሁ በሚል

[2] አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ምሁራን *apologetics* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል፣ "ምክቱ እምነት" ብለው ተርጉመውታል (ነባሩ ትርጉም የግሪኩን ቃል "ወንጌልን መመከት" ብሎታል። ጥሬ ቃሉ በዚህ መንገድ መተርጐሙ፣ ለሙያዊ ግልጋሎት የዋለው ቃል በዚህ መንገድ ለመተርጐሙ ምክንያት የሚሆን አይመስለኝም)። እኔ ይህ ቃል አስተምህሮውን በትክክል የሚወክለው አይመስለኝም። ምናልባትም፣ "ሳይቸግር ጤፍ ብድር" እንዳሆን እፈራለሁ። በስፋት እየተሠራበት ያለው ዐቅብተ እምነት የሚለው ቃል፣ የጥናቱን ዘርፍ በትክክል የሚወክለው ከሆነ፣ አዲስ ቃል መቀመሩ አስፈላጊ አይደለም። ምክንያቱም የዐቅብተ እምነት የጥናት ዘርፍ፣ የክርስትናን አስተምህሮ ከጥቃት መመከት ብቻ ሳይሆን፣ ከክርስትና ጋር የሚጻረሩ ክንቱ ምልከታዎችንም መቃወም፣ የጥናቱ ሌላው ክፍል ነው። ዐቅብተ እምነት በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ ነው። የምክቱው ወገን፣ አሉታዊ ዐቅብተ እምነት፣ በእንግሊዝኛው *negative apologetics* ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ የማጥቃቱ ወገን ደግሞ፣ አዎንታዊ ዐቅብተ እምነት *positive apologetics* በመባል ይታወቃል። በዚህ አንጻር ሲታይ "ምክቱ እምነት" የሚለው ቃል፣ ሐሳቡን በግማሽ እንጂ በሙሉ የሚወክል አይደለም። ከዚህ በፊት እየተሠራበት የሚገኘው "ዐቅብተ እምነት" የሚለው ቃል ግን፣ "ምክቱ እምነት" ከሚለው በብዙ መልኩ በብዙ የተሻለ ነው። ምክንያቱም ዐቅብተ እምነት የሚለው ቃል፣ አሉታዊውንም ሆነ አዎንታዊውን ዐቅብተ እምነት የመወከል ዐቅም አለውና። በዚህ አንጻር "ዐቀበ" የሚለው ቃል ምን ያህል ባለጸጋ እንደ ሆነ እዩልኝ:— "ዐቀበ፤ የሚጠብቅ፣ ጠባቂ፣ ተመልካች፣ ከልካይ … ጠንቅቆ ማየት፣ መመልከት፣ መጕብኘት፣ ማቆየት፣ ማዘግየት፣ መመልከት … አስጠበቀ፣ ዘበኛ አቆመ፣ ዐደራ ሰጠ"። ተገብሮ/ተደራጊ ግሥ ሲሆን ደግሞ፣ "ኦዐቀበ፤ አስጠበቀ፣ በበኛ አቆመ…ተጠነቀቀ" (አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ገጽ 703-704 ይመለከቷል)። ጥንታውያኑም ሊቃውንት ይህንኑ ቃል ነው የሚጠቀሙት፣ "ካህናት ዐቃብያነ ሕጉ ለእግዚ"።



ራሱን ለትችት በማጋለጥ፣ ከስሕተቱ ለመማር የሚፈልገው ግን እጅግ ጥቂቱ ነው።

አንድ ሰው ሌላውን ሰው በተለያየ ምክንያት ሊተች ይችላል። አንዳንዱ ባላንጣውን/ወደረኛውን ለማሳጣት በሚል ለትችት ይነሣል። አንዳንዱ ደግሞ እውነትን ከመሻት፣ ለጽድቅ ከመቈርቈር እንዲሁም ኀሰሰቡን ለማስተካከል ከመፈለግ እኳያ፣ በቅን ልቡና ሙግቱን ያደራጃል። አንዳንዱ ርእስ ጕዳዩን በውል ካለማስተዋል/ካለመረዳት በተሳሳተ ግንዛቤ ለሒስ ይጣደፋል። አንዳንዱ ከሙግቱ ጭብጥ ይልቅ፣ ሙግቱ የቀረበበት መንገድ ወይም የቋንቋ አጠቃቀም ለትችት እንዲከለፈለፍ ያደርገዋል።

አንዳንዱ ልታይ ባይ ነው። ችሎታውን ለማሳየት፣ "እኔም አለሁ" ለማለት ትችት/ሙግት ያደራጃል። ይህ ዐይነቱ ሰው፣ ሙግቱ የትኛውንም አቅጣጫ ቢከተል (ማለትም ትክክልም ቢሆን ወይም ባይሆን) ግድ የለውም። ዐላማው አስተያየት በመስጠት ሀልዎቱን ማሳወቅ፣ ዕውቅናን ማግኘት እንጂ፣ እውነትን ማሳየት አይደለምና። አለሁ የሚለውን ዐላማውን ከዳር ካደረሰ ተረጋግቶ ይቀመጣል።

ለትችት ልብን መክፈት ትልቅ ብልኅነት ነው። እሳውቃለሁ፣ አስተምራለሁ በሚባልበት መድረክ ላይ ማወቅ፣ መማር አለና። አእምሯዊ ዕድገቱ ያልተቀጨ ሰው፣ ራሱን ለትችት አሳልፎ በመስጠት እውነትን ገንዘብ ያደርጋታል። ትላልቅ የትምህርት ተቋማት ትችትን፣ ሙግትን፣ ግምገማን፣ ውይይትን ለተማሪዎቻቸው በማስተማሪያነት የሚያቀርቡት በዚህ እግባብ ነው።

ሰዎች እኛን ለማሳጣትም ሆነ፣ እኛን ለማረም ወይም ደግሞ በሌላ ስውር ዐላማ የትችት ዶፍ ሊያዘንቡብን ይችላሉ። "ይህ ሰው ለምን ለትችት ተነሣብኝ?" የሚለውን ምርምር ገታ አድርገን፣

“ትችቱ አግባብነት አለው ወይስ የለውም?”፣ “እውነትን መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም?” በሚሉት መሠረታውያን ነጥቦች ላይ ትኩረት ብናደርግ እንለመልማለን—እውነት ታለመልማለችና። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች እውነት ኖሯቸው እንኳ፣ ሌላኛውን ወገን ለማሳጣት ወይም ደግሞ በሌላ እኩይ ምክንያት ትችት/ሒስ ለመሰንዘር ሊነሡ ይችላሉ። የትችት/የሒስ ትክክለኛነት ክልብ ተነሣሥቶት *(motive)* ጋር አንዳችም ግጣም የላትም የሚባለው በዚህና በዚህ መሰሉ ምክንያት ነው። የሰውን የልብ ተነሣሥቶት *(motive)* በትክክል የሚያውቅ፣ ልብና ኩላሊትን የሚመረምረው ትልቁ እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ የሰዎችን ልብ በመመርመር፣ የልብ መነሣሣታቸው ከዚህ ወይም ከዚያ የመነጨ ነው ለማለት ዐቅም የለንም። ግምት ልናቀርብ እንችላለን፤ ግን ፍርጥም ያለ ድምዳሜ ላይ መድረስ ያስቸግራል። ግምታችን በየትኛውም አንጻር ቢወድቅ ግን (ግለሰቡ ትክክለኛ ፍላጎት ኖሮት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መሻት ተገን አድርጎ ይነሣ) እርሱ ለሙግቱ ግብዐት ብዙ ፋይዳ የለውም። ትልቁ ቍም ነገር ትችትን/ሒስን በራሱ መመርመር፣ ትክክለኛነቱ እስከ ምን ድረስ ነው የሚለውን ማጣራት የአስተንትኖው ዋነኛ ክፍል ነው።

የእኛ የኢትዮጵያውያን ባህል ትችትን የሚፈራ፣ ሒስን የሚጸየፍ ይመስለኛል። ከሙግቱ ይልቅ፣ “አንተ ማን ሆነህ ነው እኔን የምትተች” የሚለው ንግግርና አስተሳሰብ ቶሎ ይባርቅብናል፤ ብዙ ጕዳትም ያደርሳል። ይህ ደግሞ ከሙግቱ ይልቅ በሙግቱ አቅራቢና በሙግቱ ሐያሲ/ተቺ ማንነት ላይ የሚያነጣጥር ነው።

ሙግትን መጥላትና ግለሰብን መጥላት ፍጹም የተለያዩ ጕዳዮች ናቸው። የእኔ ሙግትና ትንታኔ ከወጪ ቀሪ “ቆሻሻ” ሊሆን ይችላል። ያ ማለት ግን፣ እኔ እንደ ግለሰብ “ቆሻሻ” ነኝ ማለት



አይደለም። ሙግቱ ተሳሳተ ማለት፣ እኔ እንደ ሰው ስሑት ነኝ ማለት አይደለም። ሙግትን ማበሻቀጥ ግለሰቡን ማበሻቀጥ አይደለም። ሙግትን መጣል ሙግቱን ይዞ የቀረበውን ሰው መጣል ማለት አይደለም። ስለዚህ የያዝነውን አሳብ ከእኛ ማንነት (ኑባሬያዊ ማንነት) መለየት ይኖርብናል።

እውነት የእኛን አስተሳሰብ ስትነቅፍ፣ ልንደሰት እንጂ ልንከፋ አይገባም። በመሠረቱ ስንሟገት/ስንከራከር እውነት በእኔ አንጻር ነው ያለችው፣ የአንተ ሙግት/ጭብጥ ስሕተት ነው እያልን እኮ ነው። እውነትን መውደድና ሐሰትን መጥላት ደግሞ ተገቢ ነው። እኔ “የይሖዋ ምስክሮችን” ትምህርት እምርሬ እጠላለሁ፤ ምክንያቱም አስተምህሮአቸው ስሕተት ነው ብዬ ስለማምን። እንደ ሰው፣ “የይሖዋ ምስክሮችን” መጥላት ግን ስሕተት ነው፤ ላደርገውም አይገባም። ይልቁንም የተሳሳተ አስተምህሮ ስለባ በመሆናቸው ምክንያት ልንራራላቸው ያስፈልጋል። ስወዳቸው እኮ ነው በትክክል ላነለግላቸው የምችለው። ሐኪም በሽታን “አይወድም” በሽተኛውን ስለሚወድ ግን በሽታውን ለማጥፋት የሞት ሽረት ትግል ያደርጋል። በአጠቃላይ አንድን ፅንሰ ሐሳብ፣ አስተምህሮውን ትክክል ነው ብለው ከሚያስቡ ሰዎች ወይም ትምህርቱን ከሚያራምዱ ሰዎች ለይተን ማየት ይኖርብናል።

ዐውቆ አጥፊና የዘመኑ አባይ ነባይ ትችትን እንደ ጦር ነው የሚፈራው። ሌባ ሌብነቱ ሊታወቅበት የሚሰማውን ስሜት ለመረዳት፣ እንደ እርሱ ሌባ መሆን አያስፈልግም። የደመ ነፍስ ዕውቀት *(a priori knowledge)* ይህ ዐይነቱን ጕዳይ በትክክል ያጣራልና። የሚሠራ ሰው እንደሚሳሳት እሙን ነው፤ መሳሳቱም ሲነገረው ለመታረም ከብዙ አንጻር ፈቃደኛ ይሆናል፤ ዐላማው እውነትን ወደ ሰዎች ልብ ማድረስ ነውና። ነገር ግን ለማታለል

ታጥቆ የወጣን ሰው፣ ማታለሱ ሲታወቅበት መበሳጨቱ አይቀርም። ይህ ዐይነቱ ሰው ማታለል የአእምሮ ፍልስፍናው ብቻ ሳይሆን፣ ማንነቱ ሆኗልና በዚህ አግባብ "ሌባ" የሚለው ቃል ግብሩን ብቻ ሳይሆን ማንነቱንም ይጠቅሳል።

አባይ ነባዮችም ሆኑ ደጋፊዎቻቸው፣ "አንተ ማን ስለሆንህ ነው በሌላው ላይ የምትፈርድ"፣ "እንዳይፈረድብህ አትፍረድ"፣ "አስተዋይ ግን ዝም ይላል"፣ "አምላክ በጸሎት እንጂ በውይይት አይገኝም"፣ "ጌታ በመንፈስ እንጂ፣ በአእምሮ አይታወቅም" ወዘተ በሚለው ንግግራቸው፣ በስፋት የሚታወቁ ይመስለኛል። ይህ ዐይነቱ ንግግር በአብዛኛው እውነተኛ ምርመራንና ሐቀኛ ምዘናን አጥብቆ ይጠላል። ሰዎች እነዚህን ንግግሮች የሚናገሩት፣ ራሳቸውን ከምርመራ ለመደበቅ ሲፈልጉ እንደ ሆነ መገመት እንችላለን። ለዚህ ዐይነቱ የአትመርምሩኝ መደበቂያዎች ጥሩ ምላሽ ካልሰጠን፣ የሐሰት መጫወቻ ነው የምንሆነው። ስለዚህ ይህንንና ይህን መሰል ጥያቄ በወጉ መመርመር፣ ክርስቲያናዊ ዐቅብተ እምነትን በትክክል ለመከወን ትልቅ ድርሻ አለው፤ ምክንያቱም ይህን መሰሉ አነጋገር፣ በብዙ መልኩ አእምሮንም ሆነ አንደበትን ሸብቦ የመያዝ ጽኑ ኀያል ጉልበት አለውና።

በዚህ ክፍል፣ "እንዳይፈረድብህ አትፍረድ"፣ የሚለው ሐሳብ፣ ለአትመርምሩኝ መደበቂያ ሊሆን በፍጹም እንደማይችል እንዲሁም ምን ዐይነት መልእክት እንዲያስተላልፍ ታስቦ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጋሎት ላይ እንደ ዋለ እንመረምራለን።



## ሀ. በሌላው ላይ መፍረድ ስሕተት የሚሆንባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

በራስም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ መፍረድ ስሕተት የሚሆንበት አግባብ እንዳለ ሁሉ፣ ትክክል የሚሆንበትም አካሄድ አለ። በዚህ ምዕራፍ ይህ የግራና ቀኝ አካሄድ አግባብነቱ ምን እንደ ሆነ እንመለከታለን[3]።

## 1. በግብዝነት የተሰጠ ፍርድ ውጉዝ ነው!

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን፣ በአንዲት አጥቢያ ደብር ውስጥ የቤተ ክርስቲያኒቱን ንብረት በበላይነት የሚቈጣጠር ካህን፣ "ገበዝ" ወይም "ቄስ ገበዝ" በመባል ይጠራል። በዚህ ረገድ "ሰዎች ሰግብዝና ይሾማሉ" ሲባል፣ ለገንዘብና ለንብረት አስተዳደር ዐቃቤ ንዋይ ሆነው ይተከላሉ ማለታችን ነው። እኔ ግን "ግብዝ" ወይም "ተገበዘ" የሚለውን ቃል የተጠቀምሁት በዚህ ትርጕሙ ሳይሆን፣ አርሱ ራሱ በወደቀበት ተመሳሳይ ስሕተት አንዳንዴም በበረታ ስሕተት ራሱን ትክክል አድርጎ በማቅረብ፣ በሌሎች ላይ ሒስ የሚሰነዝረውን ሰው በሚያሳይ ትርጕሙ ነው።

አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ "ነውረኛ"[4] በሚባል ኀጢአት ወድቆ፣ ምናልባትም መውደቁን ሰዎች በይፋ ተረድተው፣

---

[3] አንዳንድ መረጃዎችን ከሚከተለው መጽሐፍ ወስጃለሁ፣ *Robert M. Bowman, Jr., Orthodoxy and Heresy: A Biblical Guide to Doctrinal Discernment, (Grand Rapids, Mi.: Baker, 1992).*

[4] ቅዱሱ መጽሐፍ እንደሚል፣ የኀጢአት ሁሉ ዋጋው ዘላለማዊ ሞት ነው፤ በዚህ አገባብ ኀጢአት ሁሉ እኩል ነው ማለት እንችላለን። ቢያንስ በእኛ ማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ፣ ኀጢአት ሁሉ እኩል ውድመት ያስከትላል ማለት የሚቻል አይመስለኝም። መሳደብና መግደል እንዴት አንድ ሊሆን ይችላል። "የሥነ ምግባር መርሖ" በሚለው መጽሐፍ፣ ይህን ጉዳይ በስፋት ለመመርመር ሙከራ አድርጌ አለሁ።

በውድቀቱ ማግሥት፣ "ቅድስና ለእግዚአብሔር" በሚል ርእስ ስብከተ ወንጌል አዘጋጅቶ፣ "ተቀደሱ!" እያለ እሳት ልሶ እሳት ጐርሶ ቢናገር፣ ድርጊቱ ብዙዎችን እንደሚያበሳጭ እሙን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ፣ "ግመል እየዋጡ ትንኝ ማጥራት" (ማቴዎስ 23÷24) ወይም "በሌላው ያለውን ጉድፍ እያመለከቱ በራሳቸው ዐይን ያለውን ምሰሶ ያለመመልከት" (ማቴዎስ 7÷3) የሚባለው ዐይነት ይሆንብናል።

ይህ ዐይነቱን የሥነ ምግባር ስብከት ተቀባይነት የሚያሳጣው፣ ግለሰቡ ራሱን እያመጻደቀ፣ ሌላውን ለጽድቅ መጥራቱ ነው። ነገር ግን "ወገኖቼ እኔም ሆንሁ እናንተ በዚህ ረገድ ወድቀናል!" ቢል የመጀመሪያውን ያህል ላያንገፈግፈን ይችላል። እንደ ግብዝነትም ላንቈጥረው እንችላለን። "ትንኝን እያጠሩ ግመልን የሚውጡ" (ማቴ 23÷24) ሰዎች ግብዝነታቸው ያስቈጣን እንጂ፣ ንግግራቸው ወይም ስብከታቸው በራሱ ስሕተት ላይሆን ይችላል[5]። ለዚህም ነው፣ ጌታ "ስሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ የነገራቸው፤ ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል። ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ፤ ጠብቁትም። ነገር ግን አየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው አታድርጉ" (ማቴ. 23÷1-3)። ከዚህ የምንማረው አንድ ሰው በግብዝነት ትችት መሰንዘሩ ምቾት ቢነሣንም እንኳ፣ ትችቱ ግን በራሱ ስሕተት ላይሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ግብዝ የሆኑ፣ ልቡናቸው ንጹሕ ያልሆነ ሰዎችን በመጠቀም ሊመክረን፣ ሊዘልፈን ይችላልና ሁል ጊዜ የሚተላለፈውን መልእክት ከአስተላላፊው ማንነትና ምግባር ለይተን ጉዳዩን መመልከት ይኖርብናል። በዚህ ረገድ ሐዋርያው ጳውሎስ የሚለውን እናንብብ:—

---

[5] ንጹሕ/ንቀፋ አልባ ሕይወት ለስብከተ ወንጌል ወሳኝ የሚሆነው በዚህ አግባብ ነው (ማቴ 7÷1-5)።



"አንዳንዶች ከቅንአትና ከክርክር እንኳ ሌሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብኩታል፤ እነዚህ ወንጌልን መመከቻ ለማድረግ እንደ ተሾምሁ ዐውቀው በፍቅር ይሰብካሉ፤ እነዚያ ግን በእስራቴ ላይ መከራን ሊያመጡብኝ መስሎአቸው፣ ለወገናቸው የሚጠቅም ፈልገው፣ በቅን አሳብ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ ያወራሉ። ምን አለ ቢሆንም በሁሉ ጎዳና፣ በማመካኘት ቢሆን ወይም በቅንነት ቢሆን ክርስቶስ ይሰበካል ስለዚህም ደስ ብሎኛል" (ፊልጵ 1÷15-18)።

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ክርስቶስን ይሰብካሉ፤ አንዳንዶች ከበጎ ቅንአት፣ ሌሎች ደግሞ በጳውሎስ ላይ መከራን ለማምጣት በመፈለግ፣ አንዳንዶች ደግሞ ምድራዊ ጥቅም በመሻት ስብከተ ወንጌልን ያካሄዳሉ። ሐዋርያው ግን የልብ ፍላጎታቸውን እንጂ ስብከተ ወንጌላቸውን አልነቀፈም። እንዲያውም መሻታቸው ሞልቶ በሐዋርያው ላይ መከራ ቢመጣ እንኳ፣ ስብከተ ወንጌላቸው ግን ትክክል መሆኑን ይገልጻል። ሙግት ለማዋቀር የተነሣንበት አሳብ ጠማማ መሆኑ፣ ሙግቱ ጠማማ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሰን አይገባም።

አንዳንድ ሰዎች፣ "ሰው ሁሉ ፍጽምና የለውምና በሌሎች ሰዎች ላይ ሒስ መሰንዘር አግባብነት ይጐድለዋል" ይላሉ። ልክ ነው ማናችንም ብንሆን ፍጹምነትን የተጐናጸፍን ሰዎች አይደለንም። የምግባራችን ብልሹነት ግን፣ በሌላው ላይ የምንሰነዝረውን ሒስ/ትችት ስሑት አያደርገውም።

ልብ ልንለው የሚገባን ሌላም ነጥብ አለ፤ ይኸውም:— "በሌላው ላይ አትፍረድ" የሚሉን ሰዎች ራሳቸው፣ በእኛ ላይ እየፈረዱብን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። "አትፍረድ" የሚለው ተግሣጻቸው ራሱ ፍርድ ነው። ይኸውም "ንግግርህ ትክክል ወይም አግባብ አይደለምና አድበህ ጪምተህ ተቀመጥ" ማለት ነው።

የመጠቆም ዐቅም እንዲሁም ኀላፊነት ተሰጥቶናል። የመንገደኛውን ማንነት ማለትም ድኅነት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጉዳይ የማወቅ ችሎታ ግን አልተሰጠንም፤ መንገዱን እናውቃለን እንጂ መንገደኛውን ልናውቅ አንችልም። ጌታ የምጽአቱን ቀን በተመለከተ፣ "ይህ ለእናንተ አልተሰጣችሁም" ማለቱ አእምሮአዊ ዐቅማችን ውሱን መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ሌላው መሠረታዊ ባልሆኑ ክርስቲያናዊ ጉዮች ላይ ፍርድ መስጠት አስፈላጊ አይደለም። ለምሳሌ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ሰንበትን ስለማክበር እንዲሁም ሥጋ ወይስ አትክልት እንብላ በሚለው ጉዳይ ላይ፣ ምርር ክርር ያለ ሒስ/ትችት ውስጥ መግባት እንደማይገባን ነግሮናል (ሮሜ 14÷1-23)። ይህ ማለት ግን ጉዳዩን በጨዋ ደንብ መነጋገር አያስፈልግም ማለቱ አይደለም። በአጠቃላይ ክክልላችን እንለፍ ስንል፣ በክልላችን/ዐቅማችን በሚፈቅደው መጠን ፍርድ እንስጥ እያልን እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

## ለ. በሌላው ላይ መፍረድ ስሕተት የማይሆንባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ከላይ *(1)* ግብዝ የሆነ፣ *(2)* ግልብ የሆነና *(3)* የሰብእውያንን ዐቅም ያላገናዘበ ፍርድ ስሕተት ነው ብለናል። በአንጻሩ ደግሞ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች በግምት ውስጥ ያካተተ ፍርድ ትክክል/አግባብ ነው።

### 1. እውነቱን ከውሸት ሠናዩን ከእኩይ የሚለይ ፍርድ ቅቡል ነው!

ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲህ ዐይነቱን ብያኔ እንድናደርግ በአጽንኦት ያሳስቡናል። ይህንንም በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን በጀማ እንድናደርግ ይጠበቅብናል (ሮሜ 12÷2፡9፤



1ቆሮ 12÷10፤ 14÷2፤ 1ተሰ 5÷19-22)። እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባባት፣ እውነተኛ አስተርእዮን/መገለጥን፣ ሐሰተኛ ከሆነው መገለጥ መለየት አስፈላጊ ጉዳይ እንደ ሆነ በአጽንኦት ያሳስባሉ።

በመንፈስ ቅዱስ ተነድተናል፣ በእግዚአብሔር ተልከናል የሚሉ ነባዮች፣ ትንቢታቸውና ግልጠታቸው፣ ቀኖናዊ በሆኑት የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መመዘን፣ መገናዘብ፣ መነጻጸር የግድ ይኖርበታል (ሐሥ. 17÷11፤ 2ቆሮ 2÷1፤ 3÷2፤ 1ዮሐ 4÷1-2፤ ይሁዳ 17)።

### 2. ንስሓ በማይገቡ ኀጥኣን ላይ የሚተላለፍ ፍርድ ቅቡል ነው!

ሐዋርያትም ሆኑ ክርስቶስ ነውረኛ የሆኑ ምግባሮችን የሚፈጽሙ ክርስቲያኖች ከክርስቲያናዊ ኅብረት መታገድ እንዳለባቸው፣ በተግሣጸ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መውደቅ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል (ማቴ. 18÷15-18፤ 1ቆሮ 5÷9-13)። ምክንያቱም ይህ ዐይነቱ ምግባር የቤተ ክርስቲያንን ንጽሕና እንዲሁም ክርስቶስ የሞተለትን ክቡር ዐላማ ያክፋፋልና። ግለሰዐቹን በተግሣጸ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጣል፣ የዘላለማዊ ዕጣ ፈንታቸውን የሚወስን አይደለም። ይልቁንም ተመክረው ተዘክረው እንዲመለሱ እንዲሁም ሌሎች የእነርሱን እኩይ አካሄድ እንዳይከተሉ ለማስገንዘብ ጭምር እንጂ። ይህ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ተግሣጹ ለወደቀበት ሰው የሚጠቅም አካሄድ ነው።

### 3. ኑፋቄን በሚያስተምሩ ሰዎች ላይ የሚተላለፍ ፍርድ ቅቡል ነው!

ቅዱሳት መጻሕፍት ኑፋቄንና የኑፋቄ መምህራንን ያለአንዳች ማቅማማት በጽናት እንድናወግዝ በግልጽ ያስተምሩናል

(ሮሜ. 16÷17፤ ገላ 1÷6-9፤ 2ጢሞ 3÷16-4÷4፤ ቲቶ 3÷10-11)። እንዲያውም ኑፋቄን የሚያስፋፉ ሰዎችን በስም ጠቅሶ ማውገዝ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ (2ጢሞ. 2÷17፤ 1ጢሞ. 1÷20፤ ነሀ. 2÷19)።

ውሃ መስሎት መርዝ የሚጠጣን ሰው፣ ድርጊቱን በፍጥነትና በተቻለ መንገድ ሁሉ ማስጣል ትክክለኛ አካሄድ ነው። እውነተኛው ወንጌል የድነት መሠረት የሆነውን ያህል፣ ጠማማ ትምህርት ደግሞ የሲኦል አበጋዝ ነውና።

እንግዲያው መጽሐፍ ቅዱስ አትፍረዱ አላለም፤ ይልቁንም ፍርድ ተገቢ እንደ ሆነ፤ ተገቢ የሆነውም ፍርድ ግልብነት የሌለበት፣ ዐመፃን ያልተከተለ፣ ግብዝነት ያልተጣባው . . . በአንጻሩ እውነትን ያማከለ፣ ጽድቅን የተከተለ፣ ምርመራን መሠረት ያደረገ . . . ሊሆን ይገባዋል።

- "ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ፣ በመልክ አትፍረዱ"
  (ዮሐንስ 7÷24)
- ፍርዳችሁ ያለግብዝነት ይሁን
  (ማቴዎስ 7÷15)
- "በፍርድ ዐመፅን አታድርጉ፤ ለድኻ አታድላ፤ ባለጠጋውንም አታክብር፤ ነገር ግን ለባልንጀራህ በእውነት ፍረድ"
  (ዘሌዋውያን 19÷15)
- "አፍህን ክፈት፤ በእውነትም ፍረድ" (ምሳሌ 3÷19)



# ክፍል አራት

## "አምላክ በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!"



**እ**ንዳንድ የበሽታ ዐይነቶች በአንድ የተወሰነ አካባቢ፣ በስፋትና በመጠን ተስፋፍተው እንደሚገኙ ይነገራል። በቀዝቃዛ አካባቢ ብቻ የሚገኙ በሽታዎች እንዳሉ ሁሉ፣ ሞቃት በሚባለው የምድር ወገብ አካባቢ በስፋት ተዛምተው የሚገኙ የበሽታ ዐይነቶችም አሉ። ለምሳሌ የሕክምናው ማኅበረሰብ፣ በመጠንና በዐይነት በምድር ወገብ አካባቢ ተስፋፍተው የሚገኙትን በሽታዎች፣ "በረሓማ በሽታዎች" *(tropical diseases)* ይላቸዋል።

ኑፋቄን በመቀመምና አባይ ነባዮችን አሠልጥኖ በማሠራጨት ረገድ፣ አሜሪካንን የሚተካከል የዓለማችን አገር ያለ አይመስለኝም። በእኔ ስሌት (ግምት እንደ ሆነ ልብ ይሏል) ዘጠና ከመቶ የሚሆኑት የክርስትና እምነት አባይ ነባዮችና መናፍቃን፣ መነሻቸው ምድረ አሜሪካ ነው—"የይሖዋ ምስክሮች"፣ "የሞርሞን እምነት"፣ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን"፣ "የእምነት እንቅስቃሴ"፣ "ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት"፣ "ክርስቲያን ሳይንስ"፣ "አርምስትሮንጋውያን"፣ "ክርስቶ ዴልፊያንስ"...። እነዚህ አደገኛ ኑፋቄዎች በስፋት ተስፋፍተው እንዲሁም ተልቅ ውድመት አስከትለው የሚገኙት ግን፣ ባላደጉት ወይም በማደግ ላይ በሚገኙ አገሮች ነው።

ለዚህ ምክንያቱ እጅግ ብዙ ሲሆን፣ አስተምህሮውን በማስፋፋት ረገድ የገንዘብ ዐቅም መኖር፣ ሥነ ጽሑፍን በመሣሪያነት መጠቀም፣ ትምህርቱ በሚሠራጭባቸው አካባቢዎች ያለው ሰው በቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ በአጠቃላይ ዕውቀት ያለው ብስለት ደካማ መሆኑ እንዲሁም የእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደ ሮማውያኑ ዘመን፣ የዓለም መነጋገሪያ ቋንቋ መሆኑ አሳብን በቀላሉ በሌላው ሰው ልብ የማድረስ ችሎት እንዲኖር አድርጓል። እነዚህ እንግዲህ ከምክንያቶቹ መኻል ይመስሉኛል[1]።

በአንድ አካባቢ በመጠንና በዐይነት ፈልተው ከሚገኙ መናፍቃዊ ትምህርቶች መኻል፣ "ቅባት" የሚባለው የዚያ ወገን ነው። ይህ አስተምህሮ የተቀመመው በቀዝቃዛው ዓለም *(temperate climates)* ማለትም በምዕራባውያኑ አገሮች እንዲሁም በምዕራባውያኑ ቢሆንም፣ በብዛትና በፍጥነት በመስፋፋት ትልቅ ውድመት ያመጣው ግን፣ በመከረኛዋ አፍሪካ በተለይ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ፣ በናይጄሪያ፣ በዩጋንዳና በደቡብ አፍሪካ ነው።

[1] የሥነ ጽሑፍን ጉልበት በተመለከተ፣ "ሀረ ተምህሮታዊነት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አብሾ፣ እርሾና ጊሾ" የሚለውን የመጨረሻ ክፍል ይመለከቷል።



ይህ ትምህርት ብዙ ፈርጅ አለው። በዚህ ክፍል ይህን ከተዛራ ያልታረመ ትምህርት፣ በቃለ እግዚአብሔር እንፈትሸዋለን። ይህን ማድረግ እንብዛም አድካሚ አይደለም። ስለቅባት የሚሰጠው ትምህርት በርካታ ጓዝ እንዲሁም አውዳሚ ቅርንጫፎች ያሉት ቢሆንም፣ የትምህርቱን ግራና ቀኝ ለመመርመር ግን ከብዙ አንጻር አስቸጋሪ አይደለም—ትምህርቱ ያስከተለውን ውድመት ያህል ውስብስብ ተፈጥሮ የለውምና። በክርክሩ ዐቢይ ጭብጥ ላይ ብቻ ትኩረት ማድረግ፣ በሚከተሉት አምስት ነጥቦች ላይ እንወያያለን፤ ይኸውም:—

*(1)* የተለያዩ የቅባት ዐይነቶች አሉን?

*(2)* ቅባት ደረጃ አለውን?

*(3)* ቅባት ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው ይተላለፋልን?

*(4)* "ዕጥፍ ቅባት" የሚባል ነገር አለን?

*(5)* "እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ!" ማለት ምን ማለት ነው?

ጉዳዩን በዚሁ ቅደም ተከተል ከመመልከታችን በፊት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ቅባት የሚያስተምረውን ትምህርት በቅኝታዊ ዳሰሳ እንመልከተው።

## ብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት፣ መቀባት/ቅባት የሚለውን አሳብ ለመወከል ሁለት የዕብራይስጥ ቃላት ግልጋሎት ላይ ውለው እናገኛለን። አንደኛው "ማሺያክ" (מָשַׁח) ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ "ዛዪት" (זַיִת) ነው—በአማርኛ "ዘይት" መባሉ፣ የሴማዊ ቋንቋዎችን ተወራራሽ ጠባይ አመላካች አይመስላችሁም?

የመጀመሪያው የዕብራይስጥ ቃል፣ ሃይማኖታዊ ሥርዐትን አመላካች ሲሆን፣ ሁለተኛው ቃል ደግሞ የመካከለኛውን ምሥራቅ

የፀሐይ ሐሩር ለመከላከል እንዲሁም ተከለ ለውነትን ለመጠበቅና ለማለዋብ በአካል ላይ የሚፈለውን መዋቢያ ቅባት ያመለክታል (መዝ. 104÷15፤ ማቴ. 6÷17፤ ሩት 3÷3፤ 2ሳሙ 12÷20፤ ሕዝ. 16÷9)[2]::

ቅባት በሃይማኖታዊው ሥርዐት ውስጥ እውን ሆኖ የምናየው ከንጉሥ ዳዊትም በፊት እንዲያውም በመላው የብሉይ ኪዳን ምንባባት ውስጥ ነው (ዘሌ. 4÷3፤ 1ሳሙ. 2÷10፤ ኢሳ. 45÷1፤ ዘዳ. 28÷40፤ ሩት 3÷3፤ 2ሳሙ. 12÷20፤ 14÷2፤ 2ዜና 28÷15፤ ሕዝ. 16÷9፤ ሚኪ. 6÷15፤ ዳን. 10÷3)[3]:: ይህ ሃይማኖታዊ እንድምታ ያለው ቃል፣ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሰባ ሁለት (72) ጊዜ ጥቅም ላይ ውሎ እናገኘዋለን::

በብሉይ ኪዳን ምንባባት፣ አንድ ሰው ተቀባ (በዕብራይስጥ ማሺያኽ) የሚባለው ቃል የሚከተሉትን ትርጉሞች ወክሏል:—

1. ለተለየ ዐላማ ወይም ተግባር መሾም/መለየም:: ይህም መንፈስ ቅዱስን መቀበልንና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቁ መሆንን የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ የሚከተሉትን ምንባባት ይመለከቷል፣ ካህናት—ዘፀ. 28÷37፤ 40÷13:15፤ ዘሌ. 6÷22፤ ዘኍ. 35÷25፤ ነገሥታት—1ሳሙ. 9÷16፤ 10÷1፤ 15÷1፤ 16÷3:13 ነቢያት—1ነገ. 19÷16፤ ኢሳ. 61÷1)::
2. የእግዚአብሔርን ግርማ ሞገስ ማግኘት (መዝ. 23÷5፤ 92÷10)::
3. የእግዚአብሔር ሥልጣን ወይም መንፈስ፣ በተቀባው ግለሰብ ላይ መሆን (1ሳሙ. 16÷13፤ ኢሳ. 61÷1፤ 2ነገ. 9÷11-13)::

[2] *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Hebrew (Old Testament), electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).*

[3] ዝኒ ከማሁ::



እንግዲያው በብሉያት አንድ ሰው ተቀባ ሲባል፣ ተመረጠ፣ ተሾመ፣ ተለየ (ተቀደሰ)፣ እንዲሁም ለተጠራበት (ለተሾመበት) ሥራ ብቃትን፣ ክሂሎትን፣ ውክልናን ተጐናጸፈ ማለት ነው::

## ሐዲስ ኪዳን

በብሉያት፣ "ማሺያኽ" (מָשִׁיחַ) እንዲሁም "ዛዪት"(זַיִת) የሚሉትን የዕብራይስጥ ቃላት ተክቶ ግልጋሎት ላይ የዋለው፣ "ካሪዝማ" (χρῖσμα) የሚለው የግሪክ ቃል ነው[4]:: ይህም ቃል በሐዲስ ኪዳን የሚከተሉትን ትርጉሞች ይዞ ጥቅም ላይ ውሏል:—

1. ሰውነትን ለማለዋብ ወይም ለመንከባከብ ሲባል ሰዎች አካላቸውን የሚቀቡት ቅባት (ማቴ 6÷17፤ ሉቃ. 7÷46፤ እንዲሁም የሚከተሉትን ክፍሎች ይመለከቷል ሩት 3÷3፤ ሚኪ 6÷15፤ መዝ 23÷5)::
2. ለእንግዳ የሚደረግን ጥንቃቄና ክብር ለማሳየት (ማቴ. 26÷7፤ ሉቃ. 7÷38)::
3. አስከሬንን መቀባት (ማር. 14÷8)::
4. ድውያን/በሽተኞች ይፈወሱ ዘንድ ጸሎት ለማድረግ (ያዕ. 5÷14፤ ማር. 6÷13)::
5. መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ አንዳደረ/እንደ ኖረ ለማሳየት (2ቆሮ. 1÷21፤ 1ዮሐ 2÷20:27)::
6. ጌታ ኢየሱስን ለማሳየት (መዝ. 2÷2፤ ዳን. 9÷25:26፤ ኢሳ. 61÷1፤ ዮሐ. 1÷41፤ 4÷25-26፤ ሐሥ. 9÷22፤ 17÷2:3፤ 18÷4:28፤ ዮሐ 1÷32:33፤ ሐሥ. 4÷27፤ 10÷38)::
7. ሕዝበ ክርስቲያኑ (አማኞች ሁሉ) የተቀበሉትን መንፈስ ቅዱስ ለማመልከት (2ቆሮ. 1÷21፤ 1ዮሐ 2÷20:27)::

[4] *James Swanson, Dictionary of Biblical Languages With Semantic Domains: Greek (New Testament), electronic ed. (Oak Harbor: Logos Research Systems, Inc., 1997).*

በጭራሽ አብሮ የሚሄድ አይደለም። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ይህ ዐይነቱን እንግዳ ትምህርት የማስቆም ኀላፊነትና ሕዝቡን የማንቃት ግዴታ አለባት[10]። በዚህ አግባብ ዘይት በማፍሰስ ሰዎችን የሚቀቡ እንዲሁም “ጌታ፣ በዚህ ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ትቀባልኛለህ ብሎኛል” የሚሉ፣ የአባይ ነባዮች ትምህርት ወይም ትንቢት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም።

***ሦስተኛ፤*** በብሉይ ኪዳን የቤተ መቅደስ ዕቃዎች ይቀቡ የነበረ ቢሆንም፣ በሐዲስ ኪዳን ግን ቊሳቊስ አይቀባም። ምክንያቱም በሐዲስ ኪዳን፣ መንፈስ ቅዱስ የሚኖረው ሰው በሠራሰት ቊስ ወይም ቤተ መቅደስ ሳይሆን፣ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ናችሁ በተባሉት ክርስቲያኖች ውስጥ ነው።

***አራተኛ፤*** ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ አድርጎ ሲቀበል በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ስለሆነ፣ “እገሌ የተቀባ ሰባኪ ነው”፣ “የተቀባ ዘማሪ ነው” ወዘተ የሚሉት አነጋገሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደሉም፤ ስሕተት ናቸው።

***አምስተኛ፤*** ቅባት እንደ ጸጋ ስጦታ የሚለያይ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች እንዳሉ ቢያስተምርም፣ ልዩ ልዩ መቀባቶች/ቅባቶች አሉ የሚል ትምህርት የለውም። እንዲያውም አማኞች ሁሉ የተቀቡት ቅባት አንድ ዐይነት ቅባት ነው። መጠኑም አንድ ነው። ስለዚህ ዕጥፍ ቅባት፣ ወፍራም ቅባት ወይም ደግሞ ወርቃማ ቅባት፣ ብርማ ቅባት...የሚለው ትምህርት

---

[10] በቅርቡ አንድ ግለሰብ፣ “ዓመቱ ሳይጠናቀቅ በሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አምስት ሰዎችን ትቀባልኛለህ” የሚል ትንቢት ሲነገረው የሚያሳይ ቪዲዮ ተመለከትሁ። በመሠረቱ ያ ግለሰብ እስከ ዛሬ ድረስ፣ ወደ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን ዝር ማለት የቻለ አይመስለኝም። የሆነው ሆኖ ግን እየበሩ አንተ “ለነቢይነት፣ አንተ ለወንጌላዊነት...ተቀብተሃል” እያሉ በሰዎች ዐናት ላይ ዘይት ማፍሰስ የወንጌል ትምህርት አይደለም። የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትም ትውፊት አይደለም። ይህ እውነት ከሆነ፣ “እየዞርህ ትቀባልኛለህ” የሚለው ትንቢት ከእግዚአብሔር ሊሆን በፍጹም አይችልም።



ስሕተት ነው። ክስሕተትነቱም ባሻገር በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ድነት አግኝተዋል በተባሉት አማኞች መኻል ልዩነት የሚያበጅ፣ አማኞችን የሚያበላልጥ ነውረኛ ትምህርት ስለሆነ በግልጽ ሊወገዝ ይገባዋል።

***ስድስተኛ፤*** የተቀባ *("The Anointed One")* የሚለው ሙያዊ ቃል በተጸውዖ ስምነት የሚያመለክተው፣ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ ነው (ሉቃስ 2÷26)። ስለዚህ ሰዎችን “የተቀባ” እያሉ መጥራት ወይም ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን “የተቀባው” ብሎ መሰየም ትክክል አይደለም።

## 1. የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች አሉን?

መጽሐፍ ቅዱስ፣ አንድ ዐይነት ቅባት እንጂ፣ የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች እንዳሉ አያስተምርም። በቅባት የተመሰለውም መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ልዩ አገልግሎት (1ቆሮንቶስ 12÷5)፣ ልዩ ልዩ አሠራር (1ቆሮንቶስ 12÷6)፣ ልዩ ልዩ ስጦታ (1ቆሮንቶስ 12÷4) እንዳለ ይናገራል እንጂ፣ የተለያዩ ዐይነት ቅባቶች አሉ አይልም። ወርቃማ፣ ብርማ፣ ወዘተ የሚሉት ገለጻዎች ቢያንስ ክሐዲስ ኪዳን አስተምህሮና ከሐዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ አንጻር ድርሳነ ፈጠራ ናቸው።

በመንፈስ ቅዱስ የተቀባ ነው (2ቆሮንቶስ 1÷21፤ 1ዮሐንስ 2÷20:27)፣ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ነው (ዮሐንስ 14÷16፤ 1ዮሐ 2÷20:27)፣ በመንፈስ ቅዱስ የተጠመቀ ነው (ሐሥ. 1÷4-5፤ ሉቃስ 3÷3:16፤ 1ቆሮ 12÷13)፣ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆንነው (ዮሐ. 13÷10፤ 15÷3፤ ሮሜ 8÷9፤ ዮሐ. 3÷5) እንዲሁም በመንፈስ ቅዱስ የታተምነው ዳግም በመወለድ የእግዚአብሔር ልጆች ስለሆንን እንጂ (ዮሐንስ 7÷37-39፤ ኤፌሶን 1÷13፤ ገላትያ 3÷2፤ 2ቆሮንቶስ 1÷22፤ ኤፌሶን 4÷30)፣ በጽድቅ ከሌሎች ስለተሻልን፣ በዕውቀት ከሌሎች ስለበለጥን፣ በጥንካሬ ጽኑአን ስለሆንን ወዘተረፈ አይደለም። በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ እንዲሁም በመንፈስ

ቅዱስ ርዳታ ብቻ ክርስቲያን ሆነናል፤ ለአገልግሎት ተሹመናል። በአጠቃላይ ክርስቲያኖች የተቀቡበት ቅባት በዐይነት *(quality)* ይለያያል የሚለው ትምህርት ስሕተት ነው።

## 2. ቅባት ደረጃ አለውን?

ቅባት ደረጃ አለው፤ ከዚህም የተነሣ እያደገ ይሄዳል የሚለውን ትምህርት የሚያስተምሩ ሰዎች፣ ለትምህርታቸው ግብዐት የሚጠቀሙት የዳዊትን ታሪክ ነው። እግዚአብሔር አምላክ፣ ዳዊትን ለመጀመሪያ ጊዜ የቀባው በቤተ ልሔም በቤተሰቡ ፊት በነቢዩ ሳሙኤል አማካይነት ነበር (1ሳሙ 16፥12-13)። ሁለተኛ ጊዜ በይሁዳ ሰዎች ላይ ይነግሥ ዘንድ ዳግመኛ ተቀባ (2ሳሙ 2፥4-7)። እዚህ ጋ ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ፣ ዳዊት በይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዲሁም በነቢይ ወይም በካህን አማካይነት አልነበረም (2ሳሙ 2፥7)። በሁለተኛ ሳሙኤል 5፥3 ላይ ዳዊት ከእስራኤል ሽማግሌዎች ጋር ቃል ኪዳን ሲያቆም፣ በመላው እስራኤል ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የእስራኤል ተወካይ የሆኑት ሽማግሌዎች ሲቀቡት እንመለከታለን። እንደ ሁለተኛው ጊዜ ሁሉ፣ በዚህም ወቅት እግዚአብሔር እንዲቀቡት ሲያዝ እንዲሁም ታዋቂ ካህን ወይም ነቢይ ሲቀባው አንመለከትም።

ከእነዚህ ምንባባት በግልጥ የምንረዳው ሐቅ ዳዊት፣ በእግዚአብሔር ትእዛዝ በዕውቅ የእግዚአብሔር ነቢይ ለንጉሥነት የተቀባው አንድ ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ ነው (1ሳሙ 16፥12-3)። መጀመሪያ ከተቀባ በኋላ፣ እግዚአብሔር ደጋግማችሁ ቀቡት አላለም።

በሁለተኛ ሳሙኤል 2፥4-7 ላይ የምናነበው በጓዳ በቤተሰቦቹ ፊት የተቀባው ዳዊት፣ በይሁዳ ሰዎች ላይ ንጉሥ ይሆን ዘንድ የተቀባው ንግሥናውን ይፋ ለማድረግ ብቻ ነው። በሁተኛ ሳሙኤል 5፥3 ላይ በእስራኤል ሽማግሌዎች ፊት የተቀባው በመላው እስራኤል



ላይ ንጉሥ መሆኑን ለመግለጽ የተካሄደ ሥርዐተ ሲመት ነው። ስለዚህ የዳዊት ታሪክ፣ "መቀባት ደረጃ" አለው ለሚለው የቡና ወሬ፣ አንዳችም ድጋፍ አይሰጥም፤ ፍንጭ ጠቋሚ ነገርም አይገኝበትም።

አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ማደር በሚጀምርበት ቀን ተቀብቶአል። ስለዚህ ቅባት ደረጃ በደረጃ የሚቀቡበት ሂደት አይደለም (ሮሜ 8፥9፤ 2ቆሮ. 1፥22-23)።

## 3. ቅባት ይተላለፋልን?

ቅባት እጅ በመጫን፣ የተቀባ ሰው በቆመበት ምስባክ (አትሮኖስ ወይም ዐውደ ምሕረት) ላይ በመቆም፣ የተቀባ ሰው የጸለየበትን ጨርቅ፣ ውሃ፣ ሳሙና፣ ዘይት፣ በመቀባት ይተላለፋል የሚለው ተረት፣ ለቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት ሲበዛ እንግዳ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሞላባቸው"፣ "ወረደባቸው" ወዘተ ይላል እንጂ፣ "ተላለፈባቸው" አይልም። ቅባት ይተላለፋል የሚሉ ሰዎች ለትምህርታቸው መደገፊያ የሚያደርጉት ጥቅስ፣ በዘኍልቁ ምዕራፍ 11 ላይ ያለውን ምንባብ ነው። ነገር ግን ክፍሉ ቅባት ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው ይተላለፋል የሚል አንዳችም አሳብ የለውም።

በመሠረቱ በክፍሉ ምንባብ ላይ፣ "መንፈስ ቅዱስ" እንጂ፣ "ቅባት" የሚል አንዳችም ቃል አናገኝም። መንፈሱንም ቢሆን፣ ከሙሴ ወስዶ ለሰባዎቹ የሰጠው ራሱ እግዚአብሔር እንጂ፣ ሙሴ እጁን ስለጫነ፣ ሙሴ በቆመበት ስፍራ ስለቆሙ፣ ሙሴ የጸለየበትን ጨርቅ በእምነት ስለነኩ ወይም በሌላ መንገድ አይደለም። መንፈስ ቅዱስን ለሰዎች የሚሰጠው ልዑል እግዚአብሔር ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ቅባትን "ለማስተላለፍ" ከላይ የጠቀስናቸውን መንገዶች ሲጠቀም በፍጹም አናይም። በዚህ ምዕራፍ በቍጥር 26 እስከ 30 ባለው ምንባብ በኤልዳድና በሞዳድ ላይ፣ "መንፈስ ወረደባቸው" ይላል። ይህም የመንፈስ ቅዱስ ሰጪ ልዑል

እግዚአብሔር እንደ ሆነ፣ በቀጥታ ከአምላክ ወደ አገልጋዮቹ የሚወርድ እንደ ሆነ የሚገልጽ እንጂ፣ የሚተላለፍ እንዳልሆነ ይገልጻል። መንፈስ ቅዱስ አይቈነጠርም፣ አይባዛምም። አንዱ እንደ ነዳጅ ማጠራቀሚያ "ዴፖ" ሆኖ፣ ከእርሱ እየተቈነጠረ ለሌላው ሰው አይሰጥም። መንፈስ ቅዱስ ጌታን ባመነ ሰው ሁሉ ውስጥ ያድራል። አራት ነጥብ።

የኢየሱስ ክርስቶስን የጽድቅ ሥራ አምነው የሚቀበሉ ሰዎች፣ የእርሱ ጽድቅ የእነርሱ ጽድቅ ሆኖ እንደ ሚቈጠርላቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። የአዳም ኀጢአት አዳማውያን ወደ ሆኑ የሰው ልጆች ሁሉ እንደ ተላለፈ፣ በዚህም ምክንያት ሰዎች በግብር ኀጢአታቸው ብቻ ሳይሆን በጥንተ አብሶ (በውርስ ኀጢአት) ለሞት ተላልፈው ተሰጥተዋል። ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ የትኪ ሞት በመሞት ይህን ቤዛዊ ሥራ አምነው የተቀበሉ ሁሉ፣ የክርስቶስ ጽድቅ ጽድቃቸው ሆኖ ይቈጠርላቸዋል። ይህ በነገረ መለኮቱ ዓለም በእንግሊዝኛው *"imputation"* በመባል ይታወቃል[11]።

የእምነት እንቅስቃሴ መምህራን *"impartation"* የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል (በቍሙ መስጠት ወይም ማቀበል ማለት ነው) በመጠቀም፣ "ቅባቴን ሳጋባብህ"፣ "ስጦታዬን ሳስተላልፍብህ" ወይም ደግሞ "ለተወሰነ ጊዜ የእኔ ስጦታ በአንተ ዘንድ ይደር" የሚለውን አሳብ ሲናገሩ ይደመጣል። የጸጋ ስጦታዎችን መስጠት የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፈቃድና ችሎታ ብቻ ነው። በዚህ ዐይነቱ ተግባር ውስጥ እንዳችም የሰዎች ድርሻ የለበትም።

ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ሳያችሁ እናፍቃለሁና" ወይም "የእግዚአብሔርን ወንጌል... እናካፍላችሁ ዘንድ" ሲል ጌታ በሰጠው ጸጋ ሊያገለግላቸው መፈለጉን

[11] የሐዲስ ኪዳን ግሪክ አብዛኛውን ጊዜ "ሎጊዚዮማይ" "λογίζομαι" ሲለው፣ ዕብራይስጡ ደግሞ በአብዛኛው፣ "ራጻሕ" חָשַׁב ይለዋል ዘሌ. 7፥18፤ 17፥4፤ 2ሳሙ. 19፥19፤ ሮሜ 5፥12-19፤ ከፊልሞና 1፥18-19 ጋር ያነጻጽሯል።



የሚያሳይ እንጂ፣ የእርሱን ስጦታ ሊቈንጥርላቸው፣ ስጦታ እንካችሁ ብሎ ሊሰጣቸው እንዳሰበ የሚያሳይ እይደለም አሳብ የለም (አባክዎን የሚከተሉትን ክፍሎች ከዐውዳቸው ጋር በጥሙና ይመርምሯቸው ሮሜ 1፥11፤ 1ተሰሎ. 2፥8፤ ኤፌ. 4፥28፤ 1ጢሞ. 6፥18)።

## 4. ሁለት ዕጥፍ ቅባት አለን?

ሁለት ዕጥፍ ቅባት አለ የሚለውን ተረት የሚያስተምሩ አባይ ነባዮች፣ እዘውትረው የሚጠቅሱት የኤልያስንና የኤልሳዕን ታሪክ ነው (2ነገሥት 2)። እስገራሚው ሐቅ፣ ይህም ክፍልም ቢሆን ስለ ቅባት የሚናገረው እንዳችም ነገር ያለመኖሩ ነው፤ እንዲያውም "ቅባት" የሚለው ቃል በክፍሉ ውስጥ ተጠቅሶ እንመለከትም። ከዚህ ይልቅ ክፍሉ "ቅባት" ሳይሆን "መንፈስ" የሚለውን ቃል ነው የሚጠቀመው። በክፍሉ ውስጥ፣ "ሁለት ዕጥፍ" የሚለው ቃል የነባበት የራሱ የሆነ ታሪካዊ አግባብ አለው።

ነገሩ እንዲህ ነው፤ በብሉይ ኪዳን የበኵር ልጅ የአባቱን ዕጥፍ ንብረት በመውረስ ከሌሎቹ ወንድሞቹ የተሻለ ዕድል የሚያገኝበት አግባብ ነበረው (ዘዳግም 21፥15-17)። ኤልሳዕ የኤልያስን "ዕጥፍ መንፈስ" መፈለጉ፣ ኤልያስን በመተካት የነቢያት መሪ ለመሆን መፈለጉን የሚያሳይ ነው። ኤልሳዕ ሁለት ዕጥፍ መንፈስ መሻቱ፣ የኤልያስን ቦታ ለመተካት ያለውን ጕጕት/ፍላጎት የሚያሳይ እንጂ፣ "ሁለት ዕጥፍ ቅባት" አለ የሚል እሳብ ለማስተላለፍ አይደለም። ይህ ነው እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን ባህላዊና ሥነ ጽሑፋዊ ዐውድ ተከትሎ መተርጐም ወሳኝ ጉዳይ ነው የሚባልበት አግባብ[12]።

[12] በቅርቡ ወንድማችን ሃኒልክ አስፋው፣ *መጽሐፍ ቅዱስና የትርጓሜ ስልቱ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዴት ይነበቡ? እንዴት ይተርጎሙ? እንዴት ይተግበሩ?* በሚል ርእስ ያዘጋጀው መጽሐፍ፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን መተርጎም የራስ የሆነ

“21. ማንም እንዲጨቍናቸው አልፈቀደም፤ ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ፤ 22. እንዲህ ሲል፤ “የቀባኋቸውን አትንኩ፤ በነቢያቴ ላይ ክፉ አታድርጉ።” (1ዜና 16)

ከእነዚህ ምንባባት በግልጽ የምንመለከተው፣ “እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጅህን አታንሣ” የሚለው ገለጻ፣ በግለሰቡ ላይ አካላዊ ጥቃት ማድረስን የሚከለክል እንጂ፣ አስተምህሮአዊ ምዘናን ወይም የተተነበዩ ትንቢቶችን ከቃለ እግዚአብሔር ጋር ማመሳከርን የሚከለክል አይደለም። ስለዚህ አስተምህሮን፣ ትንቢትን፣ ትምህርትን፣ ስብከትን ወዘተ ለመገምገም ስንነሣ፣ ግምገማውን እንድናቆም የሚጠቀሰው ይህ ጥቅስ፣ አእምሮአዊ ምርምርን ወይም ፍተሻን በጭራሽ የሚከለክል አይደለም።

አንደኛ ዜና 16÷15-21 እንዲሁም በመዝሙር 105÷6-14 ባሉት ክፍሎች፣ የተቀቡ የተባሉት ርእሳን አበው ማለትም አብርሃም፣ ይስሐቅና ያዕቆብ ናቸው። የተቀባውን የአብርሃምን ሚስት ሣራን፣ ሚስቱ አድርጎ ሊወስድ ያሰበው አቢሜሌክ፣ የአብርሃምን ውሸት መርምሮ እንዳይደርስ አልተከለከለም። በዘፍጥረት 20÷7 ላይ፣ አብርሃምን “ነቢይ” ሲለው እንመለከታለን፤ በአንጻሩ በቍጥር 9-10 ባለው አቢሜሌክ የአብርሃምን ውሸት መርምሮ እንደ ደረሰበት፣ አብርሃምም የመዋሸቱ ምክንያት ምን እንደ ነበር ከ11-13 ባለው ክፍል ሲናዘዝ እንመለከታለን።

መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ ነቢይ የሆነ ሰው ትንቢቱ ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር እንዲመዘን ያስጠነቅቃል (ዘዳ. 13÷1-5፤ 18÷20-22)። በተለይ በመጨረሻው ዘመን፣ ሐሰተኛ አስተማሪዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልከው በመግባት ብዙዎችን እንደሚያሳስቱ በግልጽ ተነግሮናል። ታዲያ ይህ ዐይነቱ አደጋ በውስጣችን እንዳለ በግልጽ በተነገረበት ቦውድ፣ ትንቢት ልተንብይ ነገር ግን ትንቢቴ የአምላክ እፊምተ ቃል በሆነው በመጽሐፍ ቅዱስ አይፈተሽ ማለት እንዴት ትክክል ሊሆን ይችላል (ሮሜ 16÷17፤ 1ጢሞ. 1÷3፤ ቲቶ 1÷11፤ 3÷10-11)?



## ማጠቃለያ

በቅርቡ አምስት መቶኛ ዓመት የልደት በዓሉን ያከበረው፣ የፕሮቴስታንቱ ዓለም የወንጌል ተሐድሶ ንቅናቄ፣ ልዩ መታወቂያው ከነበሩ ዐይነተኛ ባሕርያት መኻል፣ “ቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ የአስተምህሮአችን ሁሉ ማዕከላት ናቸው” ከዚህም የተነሣ፣ “አስተምህሮዎች ሁሉ በአምላክ ቃል መመዘን የግድ ይኖርባቸዋል” እንዲሁም “ክርስቲያን፣ ያለአንዳች መካከለኛ በአምላክ ፊት በቀጥታ መቅረብ ይችላል” የሚሉት አስተምህሮዎቹ ነበሩ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከቅዱሳት መጻሕፍት ውጪ ያሉ አስተሳሰቦች ቤተ ክርስቲያንን ወረው እንዲሁም ካቶሊካዊቷ ቤተ ክርስቲያን፣ “ሰዎች አምላክ ፊት የመቅረብ ዕድል የሚያገኙት በካህናት አማካይነት ብቻ ነው”፣ “የቅዱሳት መጻሕፍትን አስተምህሮ የሚበይነው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነው” የሚለውን ትምህርት በጽኑ ለመቃወም ነበር። እንደ መራሕያነ ተሐድሶዎች፣ እያንዳንዱ አማኝ የንጉሥ ካህን ነው። ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትንም ያለአንዳች መካከለኛ በግሉ አንብቦ፣ መሠረታዊውን ትምህርት ማወቅ ይችላል።

“የአባይ ነባዮችና የመናፍቃን አስተምህሮአዊ ባሕርይ” በሚለው ክፍል ላይ በስፋት እንደ ምንመለከተው፣ መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን በመጠቀም፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንደሚያስተምሩ ነው። አባይ ነባዮችና መናፍቃን የእነርሱን ተፈላጊነት ለማላቅ እንዲሁም ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ያለእነርሱ አንዳችም ፋይዳ እንደሌለው እንዲቈጥር፣ የእነርሱን አገልግሎትና ሰብእና የሚያደምቁ በርካታ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ።

“ቅባት” የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል በመጠቀም እንዴት አድርገው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ባዕድ ትምህርት በማሾለክ የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታውያን ትምህርቶች እንደሚቃወሙ በዚህም ክፍል ለማየት ችለናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስተምረው፣ ሁላችንም በኀጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጸጋ ወድቀን የነበርን፣ ነገር ግን በአምላክ ዘላለማዊ ምሕረት፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራና በመንፈስ

ቅዱስ ርዳታ የአምላክ የጸጋ ልጆች የመሆን ሥልጣን ያገኘን ሰዎች ነን። የሆነውን ሁሉ መሆን የቻልነው በእግዚአብሔር ቸርነት ብቻ ነው። ይህን የተሳሳተ የቅባት ትምህርት፣ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በስፋት ያስተማሩት ስመ ጥር እንዲሁም አንጋፋ የሚባሉ ሰባኪያንና መጋቢያን ናቸው። እነዚህ ግለሰቦች ይህን ትምህርት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ያስተምሩት እንጂ፣ አስተምህሮው ግን ትልቅ ውድመት እንዳስከተለ በማስከተልም ላይ እንደሚገኝ ግልጽ ነው።

እንደ ቅዱሳት መጻሕፍት ትምህርት፣ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ማንኛውም ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶአል። ቅባት አምላካችን እግዚአብሔር እንደ ቸርነቱ መጠን ለልጆቹ የሚሰጠው እንጂ፣ ግለሰቦች ለአማኞች የሚያከፋፍሉት ሸቀጥ አይደለም። አንዱን ክርስቲያን ከሌላው የሚያልቁ፣ በክርስቲያኖች መካከል አጅግ አስፈላጊና አስፈሳጊ ያልሆነ ክርስቲያን የሚል ስሜት የሚፈጥሩ ትምህርቶችን ሁሉ ያለአንዳች ማቅማማት፣ በጽናት መቃወም አለብን። እኛ በአምላክ ቸርነት ብቻ ድነት ያገኘን የእግዚአብሔር የጸጋ ልጆች ነን። ይህ የክርስትና ትምህርት መሠረት ነው።

> "በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፤ ደግሞም ያተመን፣ የመንፈሱንም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው" (2ቆሮ. 1፥21-22)።
>
> "እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል" (1ዮሐ. 2፥27)።
>
> "እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፤ ሁሉንም ታውቃላችሁ" (1ዮሐ. 2፥20)።



# ክፍል አምስት

## "ፍጹም የሆነ እውነት እስከሌለ ድረስ፣ ፍጹም የሆነ ነገረ መለኮት ሊኖር አይችልም!"



በመናፍቃንና በአባይ ነባዮች ተወዳጅ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንዳሉ ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆኑ አስተሳሰቦች/አነጋገሮችም አሉ። በእነዚህ አነጋገሮች ተወግቶ የወደቀው ሰው፣ ከዐውዳቸው ተፈልቅቀው ክወጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጨቤ ምንባባት ክተወጋው ሰው የሚተናነስ አይመስለኝም። በዚህ ምዕራፍ ትክክለኛ/መልካም

*(relative)* እንዲሁም ነባራዊ *(objective)* የሚሉትን ሙያዊ ቃላት የትርጉማቸውን ዳር ድንበር ልበይን።

አንጻራዊ *(relative)* እንዲሁም ነባራዊ *(objective)* የሚሉትን ቃላት ለማብራራት የተወሰኑ ዐረፍተ ነገሮችን ልጠቀም:—

*(1)* "ወንድም ዮናስ ፋንታ ቶኒክ መጠጣት ይወዳል"

*(2)* "ሱሉልታ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች"

የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ዮናስ ስለተባለ ግለሰብ የሚናገር ነው። ግለሰቡ በፋንታ ቶኒክ ላይ ያለውን አመለካከት ይገልጻል። ስለዚህ ዐረፍተ ነገሩ ስለ ፋንታ ቶኒክ *(object)* ሳይሆን፣ ዮናስ ስለተባለው ግለሰብ *(subject)* የሚናገር ነው። ይህ አንጻራዊ *(relative)* እውነት ነው። ማንኛውም ሰው ፋንታ ቶኒክ የመውደድና ያለመውደድ ሙሉ መብት አለው። ይህ የግለሰቡ የግል ፍላጎት ነው። ማንም ሰው፣ "ምን ነካህ ጃል እንዴት ፋንታ ቶኒክ ትወዳለህ?" ሊባል አይችልም። ነገር ግን:—

*(3)* "ዮናስ ፋንታ ቶኒክ አልኮል መጠጥ ነው የሚል አቋም አለው"

ቢባል፣ "መብቱ ነው" ወይም "ትክክል ነው/እንዳሻው" ልንል አንችልም። ምክንያቱም "በፋንታ ቶኒክ ውስጥ የአልኮል ይዘት አለ ወይስ የለም?" የሚለው ጉዳይ የሚበየነው፣ በአንድ ሰው ግላዊ ፍላጎት ሳይሆን፣ ፋንታ ቶኒክ ይዞ በሚገኘው የንጥረ ነገር ይዘት ብቻ ነው። ስለዚህ የመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ትክክል ነው ወይስ ትክክል አይደለም የሚለው ጉዳይ የሚወሰነው በግለሰቡ ፍላጎት ሲሆን፣ "ሱሉልታ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች" የሚለው ግን የሚበየነው፣ በእኔ ፍላጎት ሳይሆን፣ ከተማዋ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች ወይስ አይደለም በሚለው ነባራዊ ሐቅ ነው። ስለዚህ



በዚህ አግባብ ቊጥር ሁለት ነባራዊ እውነት እንጂ አንጻራዊ አይደለም።

እንግዲያው ግብረገብን ወይም ሃይማኖትን በተመለከተ ያለው እውነት አንጻራዊ ነው ወይስ ነባራዊ/ፍጹማዊ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማብራራት ሦስት ተጨማሪ ዐረፍተ ነገሮችን እንመልከት።

*(4)* "$2+2=4$"

*(5)* "መስረቅ ትክክለኛ ምግባር ነው"

*(6)* "የዘላለም ሕይወት ለማግኘት በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛዊ ሥራ ማመን ያስፈልጋል"

የተራ ቊጥር 4 እውነትነት ወይም ውሸትነት የሚወሰነው፣ እንደ ተራ ቊጥር አንድ በግለሰብ (በማኅበረሰብ፣ በባህል ወዘተ) ፍላጎት አይደለም። እኛ ወደድንም ጠላን፣ አሜሪካ ሆንን አዲስ አበባ፣ ከዛሬ አንድ ሺህ ዓመት በፊትም ሆነ አሁን "2+2" የስሌቱ ውጤት "4" ብቻ ነው።

እንግዲያው ሥነ ምግባራዊ ፋይዳዎች (ለምሳሌ አትግደል፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ) ማለትም ቊጥር 5 እንዲሁም ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች (ማለትም ቊጥር 6) የእውነት ፋይዳቸው *(truth value)* የሚወሰነው፣ እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰብ (በማኅበረሰብ፣ በባህል ወዘተ) ፍላጎት ነው የሚለው አቋም/አመለካከት ግብረገባዊ አንጻራዊነት ይባላል።

ግብረገባዊ ፋይዳዎች (አትግደል፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ) ወይም ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ("የዘላለም ሕይወት ለማግኘት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛዊ ሥራ ማመን ያስፈልጋል") እንደ ምግብ ጣዕም በግለሰብ ወይም በማኅበረሰብ ወይም በባህል ይወሰናሉ የሚለው አቋም ግብረገባዊ አንጻራዊነት ሲባል፣ ግብረገባዊ ፋይዳዎችና ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች እንደ ሒሳብ ስሌት በጊዜ፣

በቦታና በሁኔታ እያወስኑም የሚሰው ደግሞ ነባራዊነት/ፍጹማዊነት ይባላል። እንግዲያው ግብረገባዊና ሃይማኖታዊ አስተምህሮች በአንድ ባህል፣ ወይም ግለሰብ፣ ወይም ማኅበረሰብ ወዘተ የማይወሰኑ ከሆነ፣ እነዚህ ነገሮች በምን እንጻር ይገናዘቡ ወይም እውነት ራሱ ምንድን ነው?

አንድ ነገር "ትክክል ነው" ወይም ደግሞ "ስሕተት ነው" ወዘተ ለማለት ነገሩን የምናነጻጽርበት ማገናዘቢያ (*frame of reference*) የግድ ያስፈልጋል። ረጅም አጭር፣ ትልቅ ትንሽ፣ ጠንካራ ደካማ፣ ፈጣን ዘገምተኛ ወዘተ የሚሉት ቅጽሎች/ገለጻዎች ትርጉም የሚኖራቸው፣ ማነጻጸሪያ/ማገናዘቢያ ነጥብ ወይም መሠረት ሲኖር ነው። አለያ ትርጉም ሊኖራቸው አይችልም። እንደ ፍጹማውያን/ነባራውያን ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች እንዲሁም ግብረገባዊ ፋይዳዎች በባህል፣ በሰዎች በጎ ፈቃድ፣ በማኅበረሰብ ፍላጎት ወዘተ የማይገናዘቡ ከሆነ፣ አንድን ምግባር ከምን አንጻር መዝነን ነው ትክክል ወይም ስሕተት ማለት የምንችለው የሚለው ነጥብ እውነት ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን ጉዳይ ማብራራት የግድ ይላል።

በፍልስፍናውም ሆነ በሌላው የጥናት ዘርፍ እውነት በአብዛኛው የምትብራራው፣ እኔ በግርድፉ (በሽርክቱ)፣ "ጉድኝታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ" በምለው፣ ምዕራባውያኑ ፈላስፎች *Correspondence Theory of Truth* በሚሉት ነባቤ ቃል ነበር። አሁን ግን በአብዛኛው[2] ተቀባይነት ያለው፣ ከዚህ ተጻራሪ ከሆኑት የእውነት ንድፈ ሐሳቦች መኻል አንዱ ነው። ከዚህ ውጪ ያሉት ንድፈ

[2] "በአብዛኛው" የሚለው ገለጻ ብዛትን ወይም ቍጥርን እንጂ ዐይነትን/ጥራትን አመልካች እንዳልሆነ ልብ ይሏል።



ሐሳቦች ወይም ነባቤ ቃላት እውነትን እንደ ምግብ ጣዕም ኅሊናዊ (*subjective*) የሚያደርጉ ናቸው።

ጉድኝታዊ ወይም ዝምደታዊ የእውነት ንድፈ ሐሳብ (*The Correspondence Theory of Truth*) እንድ ዐረፍተ ነገር ወይም ንግግር እውነት የሚሆነው፣ ዐረፍተ ነገሩ ከገሐዱ ዓለም (*reality*) ጋር ጥምረታዊ ወይም ጉድኝታዊ ትስስር (*correspond*) ሲያበጅ ነው[3]። ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ የተወሰኑ ሙያዊ ቃላትን ሳብራራ:—

1) እውነት ተሸካሚ (*Truth-bearer*)

እውነት ተሸካሚ የምንለው፣ የእውነት ፋይዳው (*truth value*) እውነት አለያም ሐሰት የሆነውን ዐረፍተ ነገር ብቻ ነው። "ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገር ናት" የሚለው ዐረፍተ ነገር እውነት ተሸካሚ ይባላል።

2) እውነት ፈጣሪ (*Truth-maker*)

እውነት ፈጣሪ የምንለው እውነት ተሸካሚው እውነት እንዲሆን የሚያደርገው ነገር ማለት ነው። "ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገር ናት" የሚለው እውነት ተሸካሚ እውነት የሚሆነው፣ በገሐዱ ዓለም (*reality*) ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ የምትገኝ አገር ስትሆን ብቻ ነው። ይህ "እውነት" እኛ እውነትን ከመረዳት ችሎታችን ጋር የሚያያዝ አይደለም። እኛ ይህን ጉዳይ ዐወቅን አላወቅን ጉዳዩ እውነት ነው። ለምሳሌ የጂኦግራፊ ትምህርት ያልተማረ ሰው ይህን ሐቅ ባይረዳም ወይም ካርታዎችን እንዴት ማንበብ እንዳለበት ባያውቅም፣ ጉዳዩ ግን እውነት ነው።

[3] *Truth is what corresponds to its referent.*

2) ጉድኝታዊ መስተጋብር *(Correspondence Relation)*

ስለዚህ ጉድኝታዊ መስተጋብር የምንለው፣ በእውነት ተሸካሚውና በእውነት ፈጣሪው መካከል ያለ አንድነት ነው[4]።

ስለዚህ እውነት ማለት እንደ ነገርየው የሆነ ንግግር ማለት ነው[5]። ከነሐዱ ዓለም ጋር ጉድኝት ያለው ስንል፣ ቍሳዊ ለሆኑም እንዲሁም ቍሳዊ ላልሆኑ አሳቦች *(ideas)* ማለታችን ነው። በሁለቱም መንገድ ነባራዊነት *(reality)* ያለ ሲሆን፣ እውነት *(truth)* ደግሞ ከእውነታው ጋር አንድ የሆነ ወይም ጉዳዩን በትክክል የሚወክል ጉዳይ ማለት ነው። ሐሰት ማለት ደግሞ ከነባራዊው ዓለም *(reality)* ጋር አንድ ያልሆነ ማለት ነው[6]።

## እውነት ነባራዊ ነች

እውነት ነባራዊ/ፍጹማዊ ስመሆኗ እነሆ ማስረጃዎ:—

1. እውነት አንጻራዊ ከሆነች፣ "አንጻራዊነት እውነት ነው" የሚሉ አንጻራውያን እውነት አንጻራዊ ከሆነች ይህ እውነት ሰዎች ሁሉ እንዲቀበሉት የሚገባ እውነት ሳይሆን፣ የተናጋሪው የግል አስተያየት ነው። እውነትን መሠረት ያላደረገን የግል አመለካከት መቀበል የሚኖርብን አንዳችም ምክንያት አይኖርም። "አንጻራዊነት እውነት አለ፤ የሚለው ጉዳይ አንጻራዊ በሆነ መልኩ እውነት ነው የሚባል ከሆነ" የተናጋሪውን አመለካከት መቀበል የሚኖርብን አንዳችም ምክንያት አይኖርም። ምክንያቱም ይህ አነጋገር ማዕከለ ውጋጅነት ሕግ *(Law of Excluded Middle)* የሚባለውን መሠረታዊ የሥነ አመክንዮ ሕግ ይጋጫልና።

2. አንጻራዊነት ትክክል ከሆነ፣ ዓለማችን በተቃርኖ የተሞላች ትሆናለች። ለእኔ እውነት የሆነው ነገር ለሌላው ሐሰት ከሆነ፣ ተቃራኒ ነገሮች እውነት ሊሆኑ ነው ማለት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች እንመልከት። ሀ) "በማቀዝቀዣው ውስጥ ሥጋ አለ"። ለ) "በማቀዝቀዣው ውስጥ ሥጋ የለም" የሚሉት ሁለት ዐረፍተ ነገሮች በአንድ ጊዜ፣ በተመሳሳይ ትርጕማቸው እውነት ሊሆኑ ነው ማለት ነው። ይህ ተቃርኖ ነው።

3. እውነት አንጻራዊ ከሆነች፣ አንድም ሰው ሊሳሳት፣ አንድም ሰው ትክክል ሊሆን አይችልም። እንዲያውም ትክክልና ስሕተት የሚባሉ ነገሮች ሊኖሩ አይችሉም። ምክንያቱም በምን መስፈርት ተሳስተሃል፣ በምንስ መስፈርት ትክክል ነህ ይባላል? እውነት በሰዎች ፍላጎትንና ምልከታ የሚለያይ ጉዳይ ከሆነ፣ እውነትና ስሕተት የሚባሉ ነገሮች ሊኖሩ አይችሉም።

4. አንጻራዊነት እውነት ከሆነ፣ ትምህርት ሊኖር አይችልም። ትምህርት አዳዲስ መረጃዎችን ገንዘብ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የተሳሳቱ መረጃዎችንም ማስተካከል ወይም ማስወገድ ነው። አንዳችም እውነት ወይም ሐሰት ከሌለ፣ ትምህርት ሊኖር አይችልም።

5. በአንድ ነገር ላይ ያለን ዕውቀት ፍጹም ላይሆን ይችላል፤ ዕውቀት/መረዳት ወደ ፍጽምና እያደገ የሚሄድ ጉዳይ ነውና። ይህ ግን እውነት ነባራዊ አይደለችም ማለት ስሕተት ነው። ፍጹም አርግጠኞች የምንሆንባቸው ነገሮች እንዳሉ ሁሉ፣ ፍጹም

---

[4] *Truth is what corresponds to its referent.*

[5] *Truth is "telling it like it is"*

[6] *It tells it like it is not, misrepresenting the way things are.*

እርግጠኛ የማንሆንባቸው ነገሮችም አሉ (ለምሳሌ “3+2=5” የሚለው ስሌት ውጤት ትክክል መሆኑን ፍጹም እርግጠኞች ነን። እኔ ሬሳ ላለመሆኔ እርግጠኛ ነኝ። ምክንያቱም “ሬሳ አይደለሁም” ብዬ እየተናገርሁ ሬሳ ልሆን አልችልም። “ክብ-አራት ማዕዘን” የሚባል ነገር እንደ ሌለ እርግጠኛ ነኝ፤ ምክንያቱም አንድ ነገር “ክብ ነው” ስንል በውስጡ አራት ማዕዘን አይደለም እያልን ነውና። ስለዚህ ይህ አነጋገር እርስ በርሱ የሚቃረን ንግግር ነው)። ፍጹም የሆነ እውነት የለም የሚሉ ሰዎች፣ የእውነትን ባሕርዮት እውነትን ከምናውቅበት ሂደት ጋር ይቀላቅሉታል። እውነትን የምናውቅበት መንገድ ሊለያይ ወይም ጠንካራ ወይም ደካማ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መንገዱ በመጠንና በዐይነት መለያየቱ፣ የእውነት ፋይዳውን አይቀይርም። ለምሳሌ “አዲስ አበባ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ነች” የሚለውን ጉዳይ ለማስረዳት አጥጋቢ ማስረጃ የለኝም ማለት፣ እውነታው በጭራሽ አይታወቅም ማለት አይደለም። የማስረጃ መኖርና ያለመኖር የእውነት ፋይዳውን አይቀይረውም። ቀለም አይለዩ የሆነ ሰው፣ “አረንጓዴ ቀለም ምን እንደ ሆነ አላውቅም” ስላለ አረንጓዴ የሚባል ቀለም የለም ማለት አይቻልም። እኛ እውነታውን የማወቅ ችሎታ ማግኘታችንም ሆነ ያለማግኘታችን እውነታውን ህልዎት ቅንጣት ታህል አይቀይረውም።

6. አንዳንድ ሰዎች “ጥሩ”፣ “መጥፎ”፣ “ትልቅ”፣ “ትንሽ”፣ “እውነት”፣ “ውሸት”፣ ወዘተ የሚባሉ ነገሮች ንጽጽርን ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸው፣ ፍጹም የሆነ እውነት የለም እንድንል አያስችለንም። ሰዎች ከሂትለር ጋር ሲነጻጸሩ ጥሩ ከእማሆይ ትሬዛ ጋር ሲነጻጸሩ ደግሞ መጥፎ/እኩይ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ



ጉዳይ ግን ፍጹማዊ የእውነት መስፈርት የለም እንድንል አያደርገንም። እኔ ከታላቅ ወንድሜ ጋር በቁመት ተነጻጽሬ ላንስ፣ ከታናሽ ወንድሜ ጋር ደግሞ ተነጻጽሬ ልበልጥ እችላለሁ፤ ነገር ግን ከአንዱ ጋር ተነጻጽሬ ማነሴና ከሌላው ጋር ተነጻጽሬ መብለጤ ፍጹም የሆነ እውነት ነው። ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ፍጹም የሆነ እውነት የለም እንድንል የሚያደርገን አይደለም።

7. “እውነት የማይቀያየር ቢሆን ኖሮ፣ አዲስ እውነት አይገኝም ነበር” የሚሉ ሰዎች አሉ። “አዲስ” ስንል፣ አዲስ የሆነው ለእኛ እንጂ፣ ጉዳዩማ ድሮም የነበረ ነው። ሰዎች እውነትን ፈልገው ያገኟሉ እንጂ፣ እውነትን ሊፈጥሩ አይችሉም። “ወርኀ ኅዳር 2017 ዓ.ም የተፈጠረ ወይም የተወለደ እውነት” የሚባል ነገር የለም። ነገር ግን በዚህ ቀን በርካታ እውነታዎች ሊታወቁ ይችላሉ። ይህም እውነት በየትኛውም ቦታና ጊዜ ውስጥ እውነት ነው። እውነት በአንድ የተወሰነ ወቅት ሊወለድ፣ ሊሞት፣ ሊያረጅ አይችልም። በአንድ ጊዜ እውነት ነው የሚባል ነገር፣ በማናቸውም ጊዜ እውነት ነው። ኒውተን ከመወለዱም በፊት የመሬት ስበት ነበር። ግለሰቡ ቀመሩን ዐወቀ ማለት ፈጠረ ማለት አይደለም፤ አገኘ እንጂ።

8. በአንድ ነገር ላይ ያለን ዕወቀት ጠንካራ አይደለም ማለት፣ እውነት ፍጹማዊ አይደለችም ማለት አይደለም። ሳይንሳዊ ግኝቶች ከአሮጌው እውነት ወደ አዲሱ እውነት የሚካሄዱ ሽግግሮች ሳይሆኑ፣ ለምች በርእሰ ጉዳዩ ላይ ያላቸው ዕውቀት እየጐለበተ መሄዱን የሚያሳዩ ናቸው። ፍጹማውያን ነን ማለት

ስለ እውነት ፍጹም የሆነ ወይም የተሟላ ዕውቀት አለን ማለት አይደለም።

9. እውነት አትቀየርም። እኛ በእውነት ላይ ያለን ዕውቀት ያልተሟላ ሊሆን ይችላል። በጊዜ ውስጥም እየጠራ ሊመጣ ይችላል። ይህ መሆኑ ግን እውነት ትቀያየራለች ማለት አይደለም። የሰዎች ሥነ ዕውቀት መቀያየሩ (በእውነታው ላይ ያላቸው ዕውቀት መለዋወጡ) የነባሬው እውነትነት ይቀያየራል ማለት አይደለም።

10. የሰዎች እምነት፣ እውነታውን አይቀይረውም። አንድ ሰው በየዋህነት *(sincerely)* አንድን ነገር ሊያምን ይችላል። ግለሰቡ ጉዳዩን በዚህ መልክ ማመኑ ጉዳዩን እውነት ሊያደርገው አይችልም። አንድ ሰው መሬት እንደ ሰፌድ ጠፍጣፋ ነች ብሎ በየዋህነት ሊያምን ይችላል። በየዋህነት ማመኑ ጉዳዩን እውነት ሊያደርገው አይችልም።

11. አንድ ነገር እውነት ከሆነ፣ ከእርሱ በተቃራኒ ያለው ሐሳብ ስሕተት ነው ማለት ነው። ትምህርተ ሥላሴ እውነት ከሆነ፣ ከዚህ ውጪ ያለው ትምህርት ስሕተት ነው ማለት ነው። ትምህርተ ሥላሴ እውነት ከሆነ፣ ከዚህ ትምህርት ጋር ተቃራኒ አስተሳሰብ ያላቸው፣ "ይሖዋ ምስክሮችም" ሆኑ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" አማንያን ተሳስተዋል ማለት ነው። በአንድ ወቅት በአንድ ጉባኤ፣ "ክርስትና እውነት ነው፤ በአንጻሩ ደግሞ ከእርሱ ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶች ሁሉ ስሕተት ናቸው" የሚለውን ንግግሬን ያልወደደልኝ አንድ ሰው፣ "ጽንፈኛ ነህ" አለኝ። እኔ የአንተን አስተሳሰብ ባለመቀበሌ ጽንፈኛ መሆኔ እውነት ነው። አንተም የእኔን አስተሳሰብ ባለመቀበልህ ጽንፈኛ ነህ ማለት ነው አልሁት። ጽንፈኛ የሚለው ቃል በዚህ መልኩ የሚተረጐም ከሆነ፣ ሁላታችንም ጽንፈኞች ነን። አንድ ነገር እውነት ከሆነና የእርሱ ተቃራኒው ሐሰት ከሆነ፣ እኔ ወይም ደግሞ ይህ ግለሰብ ተሳስተናል ማለት ነው። ለዚህም ነው እውነት አግላይ *(exclusive)* ባሕርይ አላት የሚባለው።

12. የሰዎች አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ዐዋጅ፣ ነባራዊ የሆነውን እውነታ አይቀይረውም፤ ሊቀይረውም አይችልም። በርካታ አባይ ነባዮችና የእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች፣ "ቃል አውጥቼብሃለሁ!"፣ "ተናግሬብሃለሁ!"፣ "ዐውጄብሃለሁ!" ወዘተ ይላሉ። የእነርሱ ዐዋጅ ወይም አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ንግግር አንዳችም ፋይዳ የለውም። ቅዱሳት መጻሕፍትም የሰዎች ንግግር እውነታውን ይቀይራል የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም[7]። ለምሳሌ አንድ ሰው፣ "መሬት ጠፍጣፋ ነች" የሚል ቃል ከአፉ ስላወጣ፣ መሬት ጠፍጣፋ ልትሆን አትችልም። አብርሃምና ሣራ "መካን ነን/ልጅ የለንም" ማለታቸው፣ ይስሐቅ እንዳይወለድ አልከለከለም። የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን፣ "ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኛለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም" ማለቷ፣ እንዳለችው እንድትሆን አልረዳትም። ይልቁንም እምላክ፣ "ጐስቋላና ምስኪንም ድኻም፣ ዕውርም፣ የተራቈትህም መሆንህን ስለማታውቅ" ሊላት እንመለከታለን (ራእይ 3፥17)።

[7] ለበለጠ ማብራሪያ፣ የዚህ መጽሐፍ ጸሓፊ፣ "የእምነት ወይስ የክህደት እንቅስቃሴ" በሚል ርእስ ከወንድም ምኒልክ አስፋው ጋር የተዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

ዘካሪያስ በስተርጅናው ልጅ ያገኘው፣ አምንታዊ ዐዋጅ በማወጁ አይደለም። እንዲያውም ኤልሳቤጥ እወልዳለሁ የሚል እምነት እንኳ እንዳልነበራት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ነገር ግን ያህ አሉታዊ ምልከታዋ/ዐዋጅዋ ልጅ እንዳታገኝ አልከለከላትም። ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው እውነት በገሐዱ ዓለም ያለን ነገር አለ ማለት ሲሆን፣ ስሕተት ደግሞ የሌለን ነገር አለ ማለት ነው። ዛሬ እንደ አንጉዳይ በዙሪያችን የፈሉት አባይ ነባዮች ይህንን ሐቅ ነው እየተጻረሩ ያሉት።

13. እውነት ባህል ዘለል ነች። አንድ ነገር እውነት ከሆነ በማንኛውም ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ ውስጥ ላሉ የሰው ልጆች እውነት ነው ማለት ነው። በዚህ አግባብ ሲታይ፣ የኢትዮጵያውያኖች ሂሳብ፣ የአሜሪካኖች ፊዚክስ፣ የእንግሊዞች ሥነ ምግባር፣ የግሪኮች ሥነ አመክንዮ የሚባል ነገር የለም። እውነታውን መጀመሪያ ያገኘው ሰው የተወሰነ አገር ዜግነት አለው ማለት፣ ግኝቱም የዚያ አገር ባልደረባ ነው ማለት አይደለም። አንዳንድ ሰዎች ይህ የምዕራባውያን ፍልስፍና፣ የአሜሪካኖች ነገረ መለኮት ወዘተ ነው ይላሉ። አንድ ፍልስፍና ወይም ነገረ መለኮት በአንድ አካባቢ ሲገኝም ሆነ ሲያብብ ይችላል፣ ይህ ማለት ግን እውነታው ቀዬአዊ/ቀበሌያዊ ነው ማለት አይደለም።

14. አንዳንድ ሰዎች እውነት ነባራዊ ነው ብለው የሚያምኑ ሰዎች ግትሮች ናቸው ይላሉ። ነገር ግን እንጻራውያንም ቢሆኑ የእኛን ተቀበሉ በማለታቸው ግትር ናቸው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ወቀሳው በሁለቱም ወገኖች ላይ የሚወድቅ ነው። ነገር ግን ሊጠየቅ የሚገባው ጥያቄ፣ “ፍጹማውያን ግትር የሆኑት በምን



ላይ ነው?” እንዲሁም “አንጻራውያን የሙጥኝ ያሉት ምኑን ነው?” በሚለው ጉዳይ ላይ ነው። ፍጹማውያን በእውነት ላይ ግትር ሲሆኑ፣ አንጻራውያን ደግሞ በሐሰት ላይ የሙጥኝ ብለዋል። ስለዚህ ወቀሳው “ግትር ለምን ሆንህ?” የሚለው ሳይሆን፣ “በምን ላይ ግትር ሆንህ?” የሚለው ነው—በእውነት ወይስ በውሸት።

15. ብዙ ሰዎች ፍጹማውያን ጠባብ ናቸው ይላሉ። 4+4 መልሱ 8 ብቻ ነው። ሌሎች እጅግ በርካታ አማራጮች የስሌቱ ትክክለኛ ምላሽ ሊሆኑ አይችሉም። ስለዚህ 8 ብቻ የሙጥኝ ማለት ጠባብ አያሰኝም። ይህ ጉዳይ ጠባብ የሚያሰኝ ከሆነ፣ ጠባብ መሆኔ ትክክል እንዲሁም አግባብ ነው። ሰዎች ሁሉ እንደ እኔው ጠባብ መሆን ይኖርባቸዋል።

## እውነት ነባራዊ መሆኗ፣ ነገረ መለኮትም ነባራዊ እንዲሆን የግድ ይላል!

ነገረ መለኮታዊ እውነት ከሌለ፣ እጅግ ተጻራሪ የሆኑ ሃይማኖቶች ሁሉ በአንድ ዐይን ሲታዩ ነው ማለት ነው። ለምሳሌ ክርስትና፣ “የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በክርስቶስ ኢየሱስ ቤዛዊ ሥራ አማካይነት ብቻ ነው” ይላል። በአንጻሩ ደግሞ የይሁዲ ሃይማኖት ይህንን አስተምህሮ አይቀበልም። ሃይማኖቶች ሁሉ ትክክል ከሆኑ፣ ይህ እርስ በርሱ የሚቃረን ዐዋጅ ትክክል ነው እንደ ማለት ነው። እውነት እርስ በርሷ ትጻረራለች ብሎ ማሰብ፣ እውነት የለም ብሎ ከማመን ጋር አንድ ዐይነት ነው።

ማናቸውም ዐይነት አስተምህሮች፣ አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት አላቸው። በአብዛኛው እውነት የሆነ ነገር አዎንታዊ ውጤት ሲያስከትል፣ ሐሰት የሆነ ነገር ደግሞ አሉታዊ ውጤት ያመጣል።

አውነትን “ወግጂልኝ!” ካልናት፣ ሐሰት መግነኑ አይቀሬ ነው። ብርሃንን ለማስወገድ ከወደድን፣ ጨለማን መጥላት አንችልም። ሥነ ምግባራዊ የሆነ አውነት ከሌለ አትግደል፣ አትስረቅ፣ አትዋሽ ወዘተ የሚሉት የሥነ ምግባር ሕግጋት አንዳችም ትርጉም አይኖራቸውም። መግደል፣ መዝረፍ፣ አስገድዶ መድፈር፣ መዋሸት፣ ስሐተት የማይሆንበት አገር ቢኖር፣ በዚህ አገር መኖር የሚፈልግ ሰው ይኖራልን? እውነትን መጥላት ሰላምን መጥላት ብቻ ሳይሆን ሕይወትንም መጥላት ነው።

## “እውነት ነባራዊ ነች የሚለው ሐሳብ መቻቻልን ያጠፋል!”

አንዳንድ ሰዎች እውነት ነባራዊ ነች ብሎ ማመን ጽንፈኝነት እንደ ሆነ እንዲሁም መቻቻል እንዲጠፋና ጽንፈኝነት እንዲያቈጠቍጥ ያደርጋል ይላሉ። ለዚህ ዐይነቱ ፍርደ ገምድል ንግግር ምክንያት የሚሆነው፣ መቻቻል ለሚለው ፅንሰ አሳብ የምንሰጠው ትርጓሜ ነው። አንዳንድ ሰዎች መቻቻል የሚለውን አሳብ የሚመለከቱት ተቃራኒ ነገሮች ሁሉ እውነት ናቸው በሚለው ትርጓሜ ነው። ተቃራኒ ነገሮች እውነት እንደማይሆኑና ሊሆኑም እንደማይችሉ ተመልክተናል። ተቃራኒ ነገሮች እውነት የሚሆኑ ከሆነ፣ ተቻቻሉ ለሚለው ሐሳብ ተቃራኒው አትቻቻሉ እስከ ሆነ ድረስ ሁለቱም ሐሳቦች ትክክል ሊሆኑ ነው ማለት ነው።

አንዳንዶች መቻቻልን የሚፈቱት ደግሞ፣ የሌላውን ሰው ሐሳብ በጥያቄ ውስጥ ካለማስገባት ጋር አያይዘው ነው። ይህም ትንተና ትክክል አይደለም። ቅዱሳት መጻሕፍት፣ “ሁሉን መርምሩ መልካሙን” ያዙ ከሚለው ምክራቸው ጋር የሚጻረር ነው ዘዳግም 13÷1-5፤ 1ዮሐንስ 4÷1፤ ገላትያ 1÷8፤ 2ቆሮንቶስ 11÷13)።



ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጥስ፣ “የሰው ልጅ የማይመረመረውን/የማይመረምረውን ሕይወት ሊኖረው አይገባም” የሚለው አነጋገሩ ሁሉን መመርመር ተገቢ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ የሰው ልጅ ግዴታም እንደ ሆነ የሚያሳስብ ነው። አገርኛውን ብሂል አንዳሻሽለው ከተፈቀደልኝ፣ “ያልመረመረ ተመነጠረ” ብል ተገቢ ነው።

ስሕተት በሆነ ነገር የገንዘብና የሕይወት መሥዋዕትነት የሚከፍሉ ሰዎች፣ ምርምርን የሕይወት መስመራቸው ባለማድረጋቸው ምክንያት በራሳቸው ላይ የሚያመጡት የጥፋትን መቅሠፍት ነው። አምሳለ መለኮት የሆኑ የሰው ልጆች እንደ ደመ ነፍሳውያኑ እንስሳት በዋል ፈሰስ ሕይወት ሊኖሩ አይገባቸውም። አእምሮን የሰጠን አምላክ፣ አእምሮን ጥለን እንድንከንፍ በፍጹም፣ በፍጹም በፍጹም አይፈልግም።

መቻቻል የሚለው ፅንሰ ሐሳብ ራሱ እውነት መኖሯን እንዲሁም እውነት ነባራዊ ባሕርይ እንዳላት ታሳቢ ያደረገ ነው። አውነት ከሌለና ሁሉም ነገር አውነት ወይም ሐሰት ካልሆነ፣ "መቻቻል” የሚለው ቃል አንዳችም ትርጉም አይኖረውም። “ቻለው” ልባል የምችለው የሚከብደኝን ነገር ግን በትዕግሥት ልሸከመው የሚገባኝን ነገር ነው።

መቻቻል እውነትን መካድ ሳይሆን፣ እውነትን አምኖ/ተቀብሎ በአንጻሩ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ትዕግሥትን ተላብሶ መኖር ነውና። መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን በፍቅር ያዟት የሚለው ንግግሩ ይህ ዐይነቱን ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ ይመስለኛል።

## “አንተ በነገረ መለኮት አንጻራዊነት ላታምን ትችላለህ፤ የአንተን አቋም ግን ልትጭንብኝ አይገባም!”

ልክ ነው፣ “የእኔ ዐይነት ነገረ መለኮታዊ አቋም ይኑርህ” ብሎ በሰዎች ላይ አካላዊም ሆነ የሥነ ልቡና ጫና ማምጣት ስሕተት ነው። የሰው ልጅ የመሰለውን የማመን ሙሉ መብት ሊሰጠው ይገባል። ትክክል ነው ብሎ ያመነበትም አቋም፣ የሚያስከትለውን አምንታዊም ሆነ አሉታዊ ውጤት፣ በሙላት የመቀበል፣ ኀላፊነትም የመውሰድ ግዴታ አለበት።

የአንተን ዐይነት አሳብ እንዲኖረኝ አታስገድደኝ የሚሉ ሰዎች ግን፣ እነርሱም የእነርሱ ዐይነት አመለካከት አንድንይዝ ጫና ሊያደርጉብን አይገባም። ከዚህም የተነሣ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ፈጽሞ የተሰጠውን ሃይማኖት” የመስበክና በዚህም አስተምህሮ ሥር የማይኖሩትን የመምከር፣ የመገሠጽ፣ አሻፈረኝ ያሉትን የማባረር ግዴታ አለባት (ይሁዳ 3፤ ማቴዎስ 18፥15-17፤ 1ቆሮንቶስ 5፥1-2)። ይህን መሠረተ እምነቷን፣ ተግባራዊ እንዳታደርግ መከልከል በፍጹም የለባትም።

ብዙ ክርስቲያኖች ይህ ዐይነቱን ንግግር ሲናገሩ ይደመጣል። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ አመክንዮ *(Logic)* በመጠቀም፣ “እኔ በግሌ ክርስቶስ አዳኝ እንደ ሆነ አምናለሁ፤ ነገር ግን አንተ አላምንም የምትል ከሆነ ትክክል ነህ”። ወይም “እኔ ክርስትና ትክክል ነው ብዬ አምናለሁ፤ አንተ ደግሞ ከዚህ በተቃረነ መልኩ ክርስትና ትክክል አይደለም ማለትህ ትክክል ነው” ማለት ይቻላልን? ነገሩን ከሃይማኖታዊ ንግግር አውጥተን ወደ ሥነ ምግባር በመውሰድ፣ “እኔ በግሌ አስገድዶ መድፈርን እቃወማለሁ፤ ነገር ግን አንተ አስገድደህ መድፈር የምትፈልግ ከሆነ መብትህ ነው” ማለት



ይቻላልን? እውነት ነባራዊ ከሆነች፣ የምናደርገው ውይይት ሁሉ እውነት በማን ዘንድ ነው ያለችው የሚለውን ጉዳይ ለማወቅ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

በዚህ አንጻር ውይይት ወይም ትምህርት ተገቢ ጉዳይ ነው። እውነት አንጻራዊ ነች የሚሉ ሰዎች፣ እውነት አንጻራዊ እንዳልሆነች፣ በማክበር እንነግራቸዋለን። ምክንያቱም እውነትን ወግድ ብለው ሐሰትን ገንዘባቸው አድርገዋልና። ቤተ ክርስቲያን እውነትን የምታውጀው፣ አምሳለ መለኮት የሆነ የሰው ልጅ የሐሰት ሰለባ እንዳይሆን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እስከ ምድር ዳርቻ ሄዳችሁ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ የሚለው እውነት ዐርነት ስለሚያወጣ፣ ሐሰት ደግሞ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ውስጥ መቀመቅ ስለሚከት ነው።

በእውነትና በሐሰት መኻል የሚገኝ ሌላ ነጻ ክልል እስከሌለ ድረስ፣ ሰዎች እውነትን አልቀበልም ካሉ ሐሰትን መቀበላቸው አይቀሬ ነው። በዚህ እግባብ እውነት አይጫንብኝ ያሉ ሰዎች ሐሰት ሊጫንባቸው የግድ ነው። ከሁለት አንዱ መጫኑ የማይቀር ከሆነም (ከእውነት ወይም ከሐሰት ውጪ ሌላ ሦስተኛ አማራጭ ከሌለ[8]) ከሐሰት ይልቅ እውነት ቢጫንብን አይሻለንምን?

## “ኑፋቄ እውነት የማይሆነው፣ ስሕተት ነው ብለን ካሰብን ብቻ ነው!”

ይህ እውነት ነባራዊ አይደለችም ይልቁንም በሰዎች አስተሳሰብ የምትወሰን ነች የሚለውን አቋም ታሳቢ ያደረገ ንግግር

[8] የእውነት ዋጋዋ እውነት ወይም ሐሰት እንጂ፣ ሌላ ሦስተኛ አማራጭ ሊገኝ አይችልም፤ መስረቅ ወይም ያለመስረቅ፣ መግደል ወይም ያለመግደል፣ ክርስቶስን ማመን ወይም ያለማመን… ከዚህ ውጪ ሦስተኛ አማራጭ ሊቀርብ አይችልም። ይህ እውነት ከሆነ አንዱን አልቀበልም የሚል ሰው ሌላውን መቀበሉ የግድ ነው። ከሁለት አንዱ መጫኑ የማይቀር ከሆነ፣ ከእውነት ጋር መወገን አይሻልምን?

ነው። ይህ ደግሞ ስሕተት እንደ ሆነ ከላይ በስፋት ለማየት ሙክራ አድርገናል። የእኛ አስተሳሰብ የእውነት ዋጋዋን ሊቀይር አይችልም። "እኔ ክርስቶስ ጌታ ነው" ብል ወይም ባልል፣ የእኔ አነጋገር ወይም አቋም ጌትነቱን ሊሰጠውም ሆነ ሊነፍገው አይችልም፣ "ሰዎች ሁሉ ሐሰተኛ ቢሆኑ እግዚአብሔር ግን እውነት ሆኖ ይኖራል" (ሮሜ *3÷4*)። መግደል እኔ ትክክል ነው ወይም ትክክል አይደለም ስላልሁ በእኔ ንግግር የእውነት ፋይዳው ሊቀየር አይችልም። ወይም የአንድ ማኅበረሰብ ወግና ትውፊት የእውነት ዋጋውን ሊወስን አይችልም። የእኛ ሥነ ዕውቀት *(epistemology)* መለያየት የኑባሬውን *(ontology)* ማንነት ቅንጣት ታህል ሊቀይረው አይችልም።



# ክፍል ስድስት

## ነቢያትና ነቢይነት በቅዱሳት መጻሕፍት



እኔ ወደ ክርስትና የመጣሁት፣ የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት መምህራን በተለምዶ፣ "የተአምራት/የኃይል ስጦታዎች"[1] በመባል የሚታወቁ የጸጋ ችሮታዎችን በተመለከተ፣ ተቃራኒ እንዲሁም የከረረ አቋም በሚያራምዱበት ታሪካዊ ወቅት ነው።

[1] ትንቢት፣ ልሳን፣ ፈውስ።